# የዕብራዊያን መልዕክት (29)

የዕብራዊያን መልዕክት በሚከተለው መንገድ ከፋፍሎ መመልከት ይቻላል፡፡

1. ምዕ 1-7 ኢየሱስ በማንነቱ ከሁሉም የበለጠ/የተሻለ እንደሆነ
   - ከነብያት ይበልጣል (1፡1-3)
   - ከመላዕክት ይበልጣል (ምዕ 1፡4-2፡18)
   - ከከሙሴ ይበልጣል (ምዕ 3)
   - ከኢያሱ ይበልጣል (ምዕ 4፡1-13)
   - ከአሮን ይበልጣል (ምዕ 4፡14-7፡28)
2. ምዕ 8-10፡18 ያለው ደግሞ ኢየሱስ በአገልግሎቱ የተሻለ መሆኑ፤
   - የተሻለ ተስፋን በመስጠት (8፡6-13)
   - የተሻለ ቤተመቅደስ (9፡1-14)
   - የተሻለ መስዋዕት (9፡15-28)
   - የተሻለ ውጤት (10፡1-18)
3. ምዕ 10፡19-13-25 የአዲስ ኪዳኑ መመሪያ ‹‹እምነት›› የተሻለ እንደሆነ፤
   - የእምነት ምስክሮች/ምሳሌዎች (ምዕ 11)
   - በእምነት መጽናት (ምዕ 12)
   - እምነት በሥራ ሲገለጥ (ምዕ 13)

በዚህ መልዕክት ውስጥ የምናያቸው ዕብራዊያን ክርስትያኖች በመንፈሳዊ ነገር ማደጋቸውን ትተው (5፡11-14) ወደኋላ እያፈገፈጉና ተስፋ በመቁረጥ ወደ ነበሩበት የህግ ሥርዓት ለመመለስ በመንሸራተት ላይ የነበሩ እንደሆኑ እንመለከታለን፡፡ እየሄዱ ያሉበት መንገድ አደገኛ መሆኑንና እጅግ ከተሻለው መንገድ ለምን መመለስ እንደሌለባቸው በተለያዩ መንገዶች ያስረዳቸዋል፡፡ ጸሐፊው አስፈላጊውን ትምህርት ከሰጠ በኋላ አብሮ የሚሄዱ ማስጠንቀቂያዎችን በማስከተል ያበረታታቸዋል፡፤

- ከቃሉ መንሸራተት እንደሌለባቸው (ከግድየለሽነት የተነሳ) 2፡1-4
- ቃሉን መጠራጠር እንዳይጀምሩ (ከልብ ጥንካሬ የተነሳ) 3፡7-4፡13
- ለቃሉ ድንዛዜ እንዳያሳዩ (ከዝለት የተነሳ) 5፡11-6፡20
- ለቃሉን ንቀት እንዳያሳዩ (ሆነ ብለው ወይም እያወቁ 10፡26-39
- ቃሉን አለመታዘዝ እንደሌለባቸው (ከእንቢተኛነት የተነሳ) 12፡14-29

ደህንነትን ችላ ስለማለትና ናቅ አድርገን እንዳናየው አምስት ማስጠንቀቂያዎችን አስፍሮልናል፡፡ ማስጠንቀቂያዎቹን ስንመለከት ከመጀመሪያው ወደ መጨረሻው በሄደ ቁጥር እየጠነከተና ሃይለኛ እየሆነ እንደሚሄድ እናያለን፡፡ ሲጀምር በ2፡1-3 ላይ አትንሸራተቱ ወይም ግድ የለሽ አትሁኑ በማለት ሲሆን በ12፡25 ላይ ማስጠንቀቂያውን ሲጨርስ እንቢ እንዳትሉ በማለት በእንቢተኛነት ተነስተው ቃሉን ለመታዘዝ እንቢ እንዳይሉ በማስጠንቀቅ ይደመድማል፡፡

አብዛኛውን ጊዜ መንፈሳዊ ችግሮች ሲከሰቱ የሚታየው ችላ ከማለት ወይም ለመንፈሳዊ ነገሮች ግድ የለሽ ከመሆን እንደሆነ ይታያል፤ ጸሎትን ችላ እንላለን፣ ቃሉን ማንበብ ችላ እንላለን፣ ከእግዚአብሄር ህዝብ ጋራ መሰብሰብን ችላ እንላለን ሌሎችንም መንፈሳዊ ነገሮች ችላ እንላለን፤ ከዚህም የተነሳ ሥፍራን መልቀቅ/መንሸራተት ይጀመራል ማለት ነው፡፡

በዚህ መልዕክት ውስጥ ጸሐፊው ያላመኑ ሰዎች ወደክርስትና እንዲመጡ ሳይሆን አማኞች ደህንነታቸውን አክብረው እንዲይዙና ወደ ፍጹምነት ማደጋቸውን እነዳያቆሙ እያበረታታ ነው፡፡

የእግዚአብሄር ህዝብ በመንፈሳዊ እድገት ላለማሳየት ሲለግምና የማፈግፈግ እርምጃ ሲጀምር እግዚአብሄር አስፈላጊውን የእርማት እርምጃ ለመውሰድ እንደሚገደድ አስጠንቅቋቸዋል፡፡ (2፡2 3፡15-19 6፡8 10፡27 12፡25)

## ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት አንድ (ለዕብራዊያን  መግቢያ)

1. ለአንዳንዶች ጳውሎስ፣ ለሌሎች ሉቃስ፣ ለሌሎች ጵርስቂላና አቂላ፣ ሌሎች ደግሞ በርናባስ እንደሚሆን ሲናገሩ፤ ለዚህም ደግሞ ሁሉም የየራሳቸውን ምክንያት የሚሉትን የመሰላቸውን ሃሳቦች ይሰነዝራሉ፡፡ እውነቱ ግን ማንነቱን ከእግዚአብሄር በቀር ሊያውቅ የሚችል ሰው የለም የሚለው ነው፡፡
2. የላኪውን ስም አለመናሩ፣ የተላከላቸውን ሰዎች ማንነት አለመናገሩና፣ በሰላምታ አለመጀመሩ ልዩ ያደርገዋል፡፡
3. ልጅነቱ ይብቃችሁና ወደ መንፈሳዊነት እደጉ፡፡ ዕብ 5፡12 እና 6፡1
4. መንፈሳዊ ችግራቸውን ለመፍታት የተጠቀመበት መንገድ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በማንነቱ፣ በአገልግሎቱና ባስተማረው የእምነት መርሆ (እምነት) ከሁሉም እንደሚሻል በማሳየት ነው፡፡
5. ጸሃፊው ብሉይ ኪዳንንና አገልጋዮቹን የማናናቅ ጉዳይ ሳይሆን የተያያዘው፤ ኢየሱስ በሁሉም መንገድ የተሻለ መሆኑን በማያወላዳ መንገድ ለማረጋገጥ ነው፡፡
6. እነዚህ ሰዎች በህይወታቸው እያሽቆለቆሉና የእግዚአብሄርን ድምጽ ችላ እያሉ እንደሄዱ አያለሁ፡፡ የተጀመረው በስህተት መውደቅ ወይም መንሸራተት ሲሆን እየጨመረ እየጨመረ ሄዶ እንዲያውም ቃሉን መታዘዝ ቀርቶ መስማት እስካለመፈለግ መድረሳቸው ይታያል፡፡ እነዚህን ሁሉ ስንመለከት አማኞች በህይወታቸው ለእግዚአብሄር ቃል የሚሰጡት ሥፍራ መንፈሳዊ እድገታቸውን እንደሚወስን መረዳት እንችላለን፡፡
7. ይህ መስዋዕት የማይደገምና ፍጹም እንደሆነ ያሳየናል፡፡
8. እያንዳንዱ የራሱን ሀሳብና ያለውን ነገር ይናገር፡፡

# ጥናት ሁለት ዕብ 1፡1-2፡4 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እግዚአብሄር የተናገራቸው ሰዎች የመጀመሪያዎቹን ‹‹አባቶቻችን›› በማለት ሲናገር የሚቀጥሉትን ደግሞ ‹‹እኛ›› ይላል፡፡ የተናገረባቸው ሁለት መንገዶች ደግሞ ‹‹ነብያት›› እና ‹‹ልጁ›› ናቸው፡፡
2. በተለያዩ ጊዜያት ሲል ለአብርሃም ከአገሩ ሳይወጣ፣ በግብጽ በባርነት ሳሉ፣ በምድረበዳ ሲዞሩ፣ ከነዓን ውስጥ፣ በንጉስ ሲተዳደሩ፣ በምርኮ ሳሉ፣ ከምርኮ ተመልሰውና የመሳሰሉትን ሲያካትት በልዩ ልዩ መንገዶች ሲል ደግሞ በአህያ፣ በህልም፣ በራዕይ፣ ኡሪምና ተሚም፣ ዕጣ በመጣልና በመሳሰሉት፡፡
3. የተናገረበት ሁለተኛው መንገድ ከመጀመሪያው መንገድ የሚበልጥባቸው ምክንያቶች፡ ሀ) ልጁ የእግዚአብሄር ክብር ነጸብራቅና የባህርዩ ትክክለኛ ምሳሌ ነው ለ) ልጁ በሃይሉ ቃል ሁሉን ደግፎ የያዘ ነው ሐ) የሐጥያትን መንጻት አስገኝቷል መ) በሰማያት በግርማው ቀኝ የተቀመጠ ነው ሠ) ከመላዕክት እጅግ የላቀ ነው፡፡
4. ዕብ 1፡4-14 ያሉት ቁጥሮች ትኩረታቸው መላዕክትንና ኢየሱስን በማወዳደር የክርስቶስን ልቀት በማረጋገጥ ላይ ነው፡፡
5. በቁ5 መሰረት ኢየሱስ የእግዚአብሄር ልጅ በመሆኑ ከመላዕክት መብለጡን ያስረዳናል፡፡ ቁ6-7 ደግሞ የማወዳደሪያ ሃሳብ አድርጎ የተጠቀመበት መንገድ አምልኮን በተመለከተ ሲሆን፤ መላዕክት አገልጋዮች ሲሆኑ ኢየሱስ ግን ስግደት የሚሰጠው እንዲያውም መላዕክቱ ሁሉ የሚሰግዱለት መሆኑን ያሳየናል፡፡
6. ይህ ክፍል መላዕክት ደህንነት የሚወርሱትን ማለትም እኛን ለማገልገል የሚላኩ አገልጋዮች ሲሆኑ፤ ኢየሱስ ግን ‹‹አምላክ ሆይ›› በማለት እግዚአብሄር አብ አምላክነቱን ያረጋገጠለት ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ ምድርን መመስረቱ፣ ሰማያትን በእጆቹ መስራቱንና ዘላለማዊነቱንና በእግዚአብሄር ቀኝ የተቀመጠ መሆኑን በመግለጽ ከመላዕክት እጅግ እንደሚበልጥ በማያወላዳ መንገድ ያረጋግጥልናል፡፡
7. በ2፡1 ላይ ያለው ማስጠንቀቂያ በምዕራፍ አንድ ላይ መልዕክቱን የተቀበልነው ከመላዕክት ሳይሆን ሰማይንና ምድርን ከፈጠረው፣ የእግዚአብሄር ልጅ ከሆነው፣ አምላክ ከሆነውና አምልኮ ከሚገባው ከኢየሱስ በመሆኑ መልዕክቱን የሰማነው እንደዚህ ካለው መልዕክተኛ መሆኑ በእኛ ላይ የበለጠ ሃላፊነትና ተጠያቂነት እንዳለብን ይጠቁመናል፡፡ አብልጦ መጠንቀቅ ሲል የብሉይ ኪዳንን ህግጋት እጅግ በጥንቃቄ ይጠብቁ እንደነበረ የታወቀ ሲሆን እኛ ደግሞ እነርሱ ካደረጉት ጥንቃቄ በላይ ማድረግ እንደሚኖርብን ያሳየናል፡፡
8. እኛ ያገኘነውን መዳን ‹‹ታላቅ መዳን›› ይለዋል፡፡ ይህ ደህንነት ታላቅ የተባለበት ምክንያት ሥላሴዎች እያንዳንዳቸው በተለያየ መንገድ የተሳተፉበት መሆኑ ነው፡፡ ጌታ ተናገረ፣ እግዚአብሄር አብ በምልክት በድንቅና በልዩ ልዩ ተዓምራት መሰከረ፣ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን በመስጠት መስክሯል፡፡
9. ይህ ማስጠንቀቂያ እኛን የሚመለከተን እኛም መልዕክቱ በእግዚአብሄር ልጅ በኩል ከደረሳቸው ሰዎች መሃል በመጨረሻው ዘመን ውስጥ የምንገኝ ስለሆንን ነው፡፡ በክፍሉ መሰረት ህግን ከተላለፉትና ከተቀጡት እስራኤላውያን በላይ በጸጋ ዘመን የወንጌልን እውነት ችላ ብለው ለሚመላለሱ የበለጠ ቅጣት እንደሚኖር ስለሚናገር የዚያ ዓይነቱ አነጋገር እንደማይሰራ እንረዳለን፡፡ ሌላውን መልስ እያንዳንዱ የራሱን ሃሳብ ይስጥበት፡፡

# ጥናት ሶስት ዕብ 2፡5-18 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ ቦታ ‹‹አንዱ›› የተባለው ሰው ስም ዳዊት ሲሆን ጥቅሱ የሚገኘውም በመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ ስምንት ውስጥ ነው፡፡
2. በመጀመሪያ ሊያሳየን የፈለገው የሰው ገጽታ፤ የሰው ልጅ እጅግ ታናሽ የሆነና እግዚአብሄር በምንም ሁኔታ ሊያስበው የሚገባ ፍጥረት አለመሆን ሲሆን ሌላው ገጽታ ግን እግዚአብሄር በፈቃዱ ያከበረው ከመላዕክት በጥቂት ብቻ ያነሰ፣ የክብርና የምስጋና ዘውድ የተጫነለት፣ ሁሉን ከእግሩ በታች ያስገዛለት መሆኑ ነው፡፡
3. ዘፍ 1፡28 ሰው በፍጥረት ሁሉ ላይ እንዲገዛ የተሰጠውን ስልጣን ባለመታዘዙና በሃጥያቱ ምክንያት እንዳጣው እናያለን፡፡
4. ኢየሱስ ከመላዕክት በጥቂት ያነሰበት ምክንያት ስለሰዎች ሁሉ ሞትን ይቀምስ ዘንድ ነው፤ ሞትን በአምላክነቱ መሞት ስለማይችል ነው፡፡ የሞትን መከራ በመቀበሉ ምክንያት የክብርና የምስጋና ዘውድ እንደተጫነለት እንመለከታለን፡፡
5. በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ማለትም በቁ8 እና በቁ9 መሃል ያለው የሃሳብ ግንኙነት እንደሚከተለው ነው፡፡ የሰው ልጅ እግዚአብሄር ካስቀመጠው የክብር ደረጃ ባለመታዘዙ ምክንያት መሞት ስለነበረበትና በአሁኑ ጊዜ ለሰው ተገዝቶ ያለ ምንም ነገር ባለመኖሩ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰዎች ምትክ መከራን በመቀበልና በመሞት ሰውን ወደ ቀደመው የክብር ሥፍራ እንዳመጣ የሚያሳየን እውነት ነው፤ ይህንን እውነት በአሁኑ ጊዜ ተገልጦ የሚታየው የሰው ወኪል በሆነው ኢየሱስ የክብርና የምስጋና ዘውድ በመጫኑ ሲሆን ለእኛ ደግሞ በእምነት መድረሻችንን የምናይበት መሆኑ ነው፡፡
6. በዚህ ክፍል የኢየሱስ መከራ መቀበል ምክንያት ሆኖ የተጠቀሰው ‹‹ብዙ ልጆችን ወደ ክብር ለማምጣት›› ነው ይላል፡፡ ኢየሱስን በዚህ ቦታ የደህንነታችን መስራች አድርጎ ነው ያስቀመጠልን፡፡
7. እኛና ጌታ የሱስ ከአንድ ቤተሰብ እንደሆንን፣ ጌታችን ወንድሞቼ ብሎ ሊጠራን እንደማያፍር፣ እኛ በእግዚአብሄር አብ ለእግዚአብሄር ወልድ ልጆቹ ሆነን የሰጠነው ሥጦታው ነን፡፡ ኢየሱስ ሥጋን መልበስ የነበረበት በሞት ላይ ሃይል ያለውን ዲያቢሎስን በሞቱ ሃይል ለመደምሰስና በሞት ፍርሃት ባርነት የታሰሩትን ደግሞ ነጻ እንዲያወጣ ነው፡፡
8. ምዕራፍ አንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ተወዳዳሪ የሌለው ከመላዕክት ሁሉ የሚበልጥ አምለክ መሆኑን ወይም መለኮታዊ ገጽታውን ሲያሳየን፤ ምዕራፍ ሁለት ግን ኢየሱስ ከመላዕክት አንሶ የነበረበትን ጊዜ ማለትም ሰብዕናው ላይ በማተኮር እንደሆነ እንመለከታለን፡፡
9. ያለንበት ሁኔታ ተስፋ የሚሰጥ እንኳን ባይሆን ኢየሱስ ከብሮና ከፍ ብሎ ማየት ከቻልን እኛም እርሱ ያዘጋጀልንን ክብር እንደምንወርስ እርግጠኛነት ይኖረናል ማለት ነው፡፡

# ጥናት አራት ዕብ 3፡1-6 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ሶስቱ መጠሪያዎች፡ የሰማያዊ ጥሪ ተካፋዮች፣ ቅዱሳንና፣ ወንድሞች የሚሉት ናቸው፡፡ ‹‹ወንድሞች›› ሲል የጸሃፊው ወንድሞች መሆናቸውን መግለጫ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ዕብ 2፡11 እንዳየነው የኢየሱስ ወንድሞች መሆናቸውንም ማሳሰቢያ ሊሆን ይችላል፡፡
2. ኢየሱስ ለእነዚህ ሰዎች የእምነታቸው ሃዋርያ ነው፣ ኢየሱስ ለቅዱሳኑ ሊቀ ካህናቸው ነው፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ ‹‹ኢየሱስን አስቡ›› ሲል ሁለት ነገሮችን ያጠቃልላል፡፡ አንደኛው በምዕ 1እና 2 ውስጥ የተናገራቸውን መለኮታዊነቱን፣ ቅድስናውን፣ የሞትን ሃይል መደምሰሱን፣ የሃጥያት ሥርየት ማስገኘቱንና የመሳሰሉትን ሁሉ ማሰብ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ እነርሱ በጊዜው በሚያልፉበት ችግርና በሁኔታዎች ላይ ሳይሆን ዓይኖቻቸውን በእርሱ ላይ ማድረግ እንደሚኖርባቸው ማሳሰቡ ነው፡፡ ቀሪውን ጥያቄ መልስ በየግል ይመልሱት፡፡
3. ሙሴና ኢየሱስ የሚመሳሰሉበት ነገር ሁለቱም በእግዚአብሄር ቤት ላይ ታማኝ መሆናቸው ነው፡፡ የሙሴን ታማኝነት የመሰከረው እግዚአብሄር ራሱ ነው፡፡ (ዘሁ 12፡7) ሙሴ ያገለገለበት ቤት ተብሎ የተጠቀሰው የእስራኤል ቤት(የእስራኤል ህዝብ ነው፡፡)
4. ቁ3 ላይ ሙሴን ያቀረበው እንደ ቤት ሲሆን ኢየሱስን ደግሞ እንደቤቱ ሰሪ አድርጎ ነው፡፡ ኢየሱስ ታማኝነቱን ያስመሰከረው፤ ከአባቱ ፈቃድ ውጭ አንዳችም አያደርግም ነበረ ዮሐ4፡34፣ ለመስቀል ሞት እንኳን የታዘዘ ነበረ ፊሊ 2፡8 አባቱ የሰጠውን ስራ በታማኝነት ፈጽሞ አከብሮታል ዮሃ 17፡4
5. ታማኝ ስንል፤ ቃሉን የሚጠብቅ፣ በየጊዜው የማይቀያየር፣ አደርጋለሁ ያለውን የሚያደርግ፣ እውነተኛና የመሳሰሉትን እምነት ለመጣል የሚያስችሉንን ነገሮች ሁሉ የያዘ ቃል ነው፡፡ ከእኛ ጋራ ባለው ግንኙነት አንጻር ሙሉ የህይወት ተስፋችንን የጣልነው በእርሱ ላይ ስለሆነ የእርሱ ታማኝ ሆኖ መገኘት ለእኛ እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ ያለበለዚያ ተስፋ ያደረግንበት ነገር ሁሉ ይሁን አይሁን እርግጠኞች ልንሆን አንችልም፡፡
6. ይህ ሙሴ ስለወደፊት ይመሰክር የነበረው ነገር ስለክርስቶስ ሲሆን ታማኝ ያሰኘውም አንዱ ነገር የሚመሰክረው ስለራሱ ሳይሆን እንደ መጥምቁ ዮሐንስ ከፊቱ ስለሚመጣወ መሲህ ነበረ፡፡ ቁ5-6 ያለው ክፍል ሙሴ በእግዚአብሄር ቤት ላይ እንደ ታማኝ አገልጋይ ሲጠቀስ፣ ኢየሱስ ግን እንደ ታማኝ ልጅ ተጠቅሷል፡፡
7. በቁ6 ላይ የእግዚአብሄር ቤት በመባል የተጠቀሰው ቤተ ክርስትያን ስትሆን ይህችንም ቤት እንደሚሰራ በማቴዎስ 16፡18 ላይ የተናገረው ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡
8. ተስፋውን አጥብቀን መያዛችን የሚያረጋግጥልን እውነት፤ በቁ6 መጨረሻ ላይ እንደምንመለከተው የክርስቶስ ማደሪያ ወይም ቤቱ መሆናችንን ነው፡፡ 2ኛ ቆሮ 13፡5፣ 1ኛ ዮሐ 2፡19ትን አንብብ፡፡ ዕብ3፡14 ትንም ስናነብ ይህንንው ሃሳብ በሌላ መንገድ የሚናገር እንደሆነ ይታያል፤ ከመጀመሪያው የያዝነውን እምነት አጽንቶ መያዝ ከክርስቶስ ጋራ እውነተኛ ተካፋዮች መሆናችንን ያረጋግጣል ማለት ነው፡፡
9. እያንዳንዱ የራሱን ሃሳብ እንዲገልጥ ጊዜ ይሰጠው፡፡

## ጥናት አምስት ዕብ 3፡7-19 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በጊዜው እየተናገረ ያለው ለእብራዊያን ክርስትያኖች(አይሁዶች) ሲሆን የሚናገረው ደግሞ ከግብጽ ወጥተው በምድረበዳ ስለወደቁት አባቶቻቸው ነው፡፡
2. በዚህ ክፍል የተሰጠው ዋነኛው ማስጠንቀቂያ የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ ስንሰማ ልባችንን እንዳናደነድን ነው፡፡ ለዚህም ምሳሌዎችን በመስጠት እያንዳንዱ ከራሱ ህይወት ጋራ እያያያዘ ይናገር፡፡
3. ‹‹ተፈታተኑኝ›› ሲል የእግዚአብሄርን ችሎታና መልካምነት ጥያቄ ስለሆነባቸው ነው፡፡ ሰዎች ድንቅና ተዓምራቶችን ማየታቸው ወደ እምነት ያመጣቸዋል ማለት እውነትነት ያለው አመለካከት እንዳልሆነ ያሳየናል፡፡
4. የሰዎቹ ልብ ማደንደን የአንድ ጊዜ ነገር እንዳልሆነ የሚያሳየን ‹‹ልባቸው ሁልጊዜ ይስታል›› የሚለውና፤ ያደረግሁትን ሁሉ ለአርባ ዓመት አዩ የሚለው ይገኙበታል፡፡ ዕረፍት ተብሎ የተጠቀሰው የከነዓን ምድር መግባት ነው፡፡
5. በዚህ ክፍል የተሰጣቸው ምክር፡ ከህያው እግዚአብሄር የሚያስኮበልል፣ ሃጥያተኛ ልብ እንዳይኖራቸው እንዲጠነቀቁ ነው፡፡ ትኩረት ተደርጎበት የምናየው ብልት ልባችን ነው፡፡
6. ክፍሉ የሚናገረው ስለ አንድ አይነት ሰዎች ሲሆን ያልገቡበትም ምክንያት አለማመን እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡ ያለማመናቸው የሰፈረበት ክፍልም ዘኁ 13 እና 14 ላይ ነው፡፡
7. እግዚአብሄር ሲናገር ሰምቶ ያለመታዘዝ የልብ ድንዳኔን ያስከትላል፡፡ ይህ አንዱ መልስ ሊሆን ይችላል ነገር ግን በተለያየ መንገድ ሊመለስ ይችላል፡፡
8. ከልብ ድንዳኔ እንድንጠበቅ በመፍትሄነት የሰጠን እርስ በእርሳችን እንድንጽናና ሲሆን ይህንንም ማድረግ የሚኖርብን በየቀኑ ነው፡፡ ይህንን ማድረግ መጀመር የሚኖርብን ዛሬውኑ ሳንውል ሳናድር ሲሆን በተጨማሪም ደግሞ አንገብጋቢነቱንና ዛሬ እንጂ ነገ የእኛ እንዳልሆነም ያሳየናል፡፡
9. እያንዳንዱ በግሉ ይመልስ፡፡

## ጥናት ስድስት ዕብ 4፡1-13 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. የዚህ ቁጥር ማስጠንቀቂያ ለዚህ እረፍት ሳንበቃ እንዳንቀር እንድንጠነቀቅ ሲሆን ማስጠንቀቂያው የተሰጠውም 3፡18-19ን በመመርኮዝ በአባቶቻቸው የደረሰውን በማሳየት መልዕክቱን ለሚቀበሉት አማኞች ነው፡፡
2. እነዚያ እያለ በዚህ ክፍል የሚናገራቸው በምድረበዳ የቀሩትን አባቶቻቸውን ነው፡፡ ለሁለታችንም ተሰበከ የሚለው የምስራች ቃል ደግሞ የተለያዩ ሰዎች ልዩ ልዩ ሃሳቦችን ይሰጣሉ፤ በእኔ አመለካከት የምስራች የሚለው የክርስቶስን ወንጌል ማለት ሳይሆን ለአባቶቻቸው ማርና ወተት ወደምታፈስ ምድር ገብተው እንደሚያርፉ የተገባላቸውን ተስፋ ሲሆን እኛ ደግሞ በክርስቶስ የሚገኘው የዘለዓለም እረፍት ሲያነጻጽር ነው፡፡
3. የእግዚአብሄር ቃል ጥቅም የማይኖረው በእምነት ካልተዋሃደ ነው፡፡ የማዋሃዱ ሃላፊነት የተጣለው በሰሚዎቹ ላይ ነው፡፡
4. የእረፍቱ ባለቤት እግዚአብሄር ነው ምክንያቱም ቁ3፣ 5 ና 10 ላይ የእርሱ እንደሆነ ይነግረናል፡፡ ወደዚህ እረፍት መግባት የሚከለክለው አንድ ነገር አለማመን ሲሆን፤ የሚገባበት ቁልፉ ደግሞ እምነት እንደሆነ ይታያል፡፡
5. እነዚህ አባቶች የተነገራቸውና አንዳንዶቹ የገቡበት እረፍት ወደፊት ለሚመጣው እውነተኛ እረፍት ምሳሌና ጥላ ስለሆነ ወደ እውነተኛው እረፍት የሚያስገባው ኢያሱ ሳይሆን ኢየሱስ ስለሆነ ነው፡፡
6. ቁ1 ድንና 11ድን ስናቀናጅ የሚከተለውን ማለት እንችላለን፡፡ ወደ እግዚአብሄር እረፍት እንዳንገባ ከሚያደርግ ነገር ማለትም ካለማመን መጠንቀቅ ብቻ ሳይሆን ወደዚህ ለእግዚአብሄር ህዝብ ወደተዘጋጀው እረፍቱ ለመግባት መትጋት እንደሚኖርብን ማወቅ ያስፈልገናል፡፡
7. ቃሉ ህያው ነው፣ የሚሰራ ነው፣ በሁለት በኩል ስለት ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ ስለታም ነው… ወዘተ፡፡ የተቀረውን ጥያቄ እያንዳንዱ የራሱን ይናገርና ለምን የሚለውን ጥያቄ አስከትል/ይ፡፡
8. ዛሬ በእኛ ዓይን የሰዎችን ህይወት ስንመለከት ብዙ ስህተቶችን ልንሳሳት እንችላለን፤ ማለትም አንዳንዶችን በውጫዊው በሚያሳዩን ነገሮች እጅግ መንፈሳዊ፣ ለእግዚአብሄር የሚቀኑና ለመንፈሳዊ ነገር የሚተጉ አድርገን ልንመለከታቸው እንችላለን፤ ሌሎችን ደግሞ አይ ይህስ እንኳን መንግስተ ሰማያት ውስጥ መግባት ይቅርና ደጁንም የሚረግጥ እንዳሆነ የደመደምንላቸው ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ፤ ሆኖም የእኛ ተልዕኮ የሰዎችን ልብ መመርመር ሳይሆን የራሳችንን ልብ መመርመር ሲሆን የሰውን ሁሉ ልብ በመመርመር ትክክለኛ ፍርድ የሚሰጥ እርሱ ብቻ መሆኑን ሊያስገነዝበን ነው፡፡
9. የመጀመሪያው አማኝ ሁኔታዎችን ሁሉ በራሱ መታገል አቁሞ በእግዚአብሄር ላይ ሙሉ በሙሉ ተደግፎ ሲኖር ወደ እግዚአብሄር እረፍት ገባ ማለት ይቻላል፤ ይህም ቁ10 ‹‹እርሱም ደግሞ ከሥራው ያርፋል›› ከሚለው ሃሳብ ጋራ ይስማማል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በዘመን ፍጻሜ ሃዘንና ጭንቀት ሳይኖር ራዕይ 14፡13 በሚናገረው ዘላለማዊ እረፍት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የተቀረው በየግል ሃሳብ ይሰጥበት፡፡

# ጥናት ሰባት ዕብ 4፡14-5፡10 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ ክፍል ኢየሱስ ሊቀ ካህን ተብሎ ነው የተጠራው፡፡ የእርሱ ክህነት ታላቅ ያሰኙት ምክንያቶች፤ ወደ ሰማያት ያረገ መሆኑና የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑ ናቸው፡፡
2. በዚህ ክፍል ውስጥ የተሰጧቸው ሁለት ምክሮች/ትዕዛዛት፤ የመጀመሪያው እምነታቸውን አጥብቀው እንዲይዙ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንዲቀርቡ ነው፡፡ እምነታቸውን አጥብቀው እንዲይዙ በምክንያትነት የቀረቡት ሃሳቦች፤ ታላቅ ሊቀ ካህን ስላላቸውና ይህም ካህን ርህሩህ መሆኑ ናቸው፡፡
3. ዕብ 4፡15 ላይ ያለው ሃሳብ ኢየሱስ እያንዳንዳችን ያለፍንባቸውን ጥቃቅን ፈተናዎች ሁሉ በህይወቱ አልፈዋል ማለት ሳይሆን አጠቃላይ በሆነ መልኩ ያለፈበትን ሲገልጥ ነው፤ ለዚህም ማቴ 4፡1-10 ያሳለፋቸውን ፈተናዎች ስንመረምር መ/ቅዱስ በ1ኛ ዮሐ 2፡16 ላይ የሥጋ ምኞት፣ የአይን አምሮትና የኑሮ ትምክህት ተብለው የተጠቀሱትን ፈተናዎች ሁሉ ተለማምዷቸዋል ማለት ነው፡፡
4. ምህረትና ጸጋ የሚገኙት ከጸጋው ዙፋን ሥር ብቻ ነው፣ ምህረትና ጸጋ አብዝቶ ሊያስፈልጉን የሚችሉበት ጊዜያት መኖራቸው፣ ምህረትንም ሆነ ጸጋን ለመቀበል የምንችለው በእምነት ስንቀርብ ብቻ መሆኑ፣ ቀድሞ ማንም እንዳይቀርብ ተብሎ ለሙሴ የተነገረው ዘሬ ለእኛ ወደ ዙፋኑ መቅረብ የልጅነት ስጦታችን መሆኑ ሁሉ ትምህርቶች ናቸው፡፡
5. ሊቀ ካህን የሚመረጠው ከሰዎች መካከል መሆን አለበት፣ ርህራሄን የተሞላ ሊሆን ይገባዋል፣ ክህነቱን ከእግዚአብሄር መቀበል አለበት፡፡ የሥራ ድርሻው ደግሞ የእግዚአብሄር በሆነው ነገር ላይ ሰዎችን ወክሎ ስለሃጥያታቸው መባንና መሥዋዕትን ያቀርባል፡፡ ሊቀ ካህን ለሰዎች ርህራሄን ሊያሳይ ይችላል ተብሎ የሚታመነው እርሱ ራሱ ድካም ያለበትና እንደሌሎቹ ስለሚስት ነው፡፡
6. ክርስቶስ የሊቀካህንነትን መስፈርት የሚያሟላው፡ ቁ5-6 በእግዚአብሄር መሾሙን፣ 2፡14 እንደ እኛ ሰው መሆኑን ሲጠቁመን፣ ዕብ 4፡15 ደግሞ ርህራሄን የተሞላ ለመሆኑ ማረጋገጫን ይሰጠናል፡፡ ከእነዚህ ክፍሎች በአሮንና በኢየሱስ መካከል የምናየው አንድ ትልቅ ልዩነት አሮን ስለራሱ ሃጥያት መስዋዕት ያቀርባል፤ ኢየሱስ ግን ይህንን ማድረግ አያስፈልገውም፡፡
7. የኢየሱስ ጸሎት ከሞት እንዲያድነው ነበረ፡፡ መልስ ያገኘበትንም ምክንያት ሲናገር፤ ፍጹም ትሁት ሆኖ በመታዘዙ ነው ይላል፡፡
8. የመጀመሪያው ትምህርት በመታዘዝ የጸሎት መሰማት እንዳለ፣ ሁለተኛው በመከራም መታዘዝን መማር እንደሚቻልና፣ ሶስተኛው ደግሞ በመታዘዝ ደህንነት እንደሚገኝ ያስተምሩናል፡፡
9. ይህ ክፍል ስለ ሊቀ ካህናችን የሚያሳየን ገጽታ ርህራሄውን ሲሆን፤ ሃሳቦቹን ሁሉ ጨምቀን ስናያቸው ሊቀ ካህኑ ኢየሱስ እኛን በመከራችን የመርዳት ችሎታ ያለው ብቻ ሳይሆን ልቡም ለእኛ የሚራራ እንደሆነ መረዳት እንችላለን፡፡ ሌላው በየግል ይመለስ፡፡

# ጥናት ሰምንት ዕብ 5፡11-6፡3

1. ‹‹ስለዚህ ጉዳይ›› የተባለለት ስለ መልከ ጼዴቅ ሹመትና ሊቀ ካህንነት ነው፡፡ በሰፊው ለመናገር ያልቻለበት ምክንያትም ሰዎቹ ለመማር ዳተኞነት ስለሚታይባቸው ነው፡፡
2. እነዚህ ሰዎች ሊገኙበት የሚገባቸው ስፍራ የአስተማሪነት ደረጃ ሲሆን፤ አሁን ያሉበት ሥፍራ ግን በተማሪነት ብቻ ሳይሆን ገና መንፈሳዊ ሀ ሁ የሚያስተምራቸው ሰው ነው የሚያስፈልጋቸው፡፡
3. ጸሐፊው በአሁኑ ጊዜ አስተማሪ አያስፈልጋችሁም ነበረ ማለቱ ሳይሆን የሚላቸው፤ በአሁኑ ጊዜ እንደ አዲስ አማኝ የክርስትናን የመጀመሪያ ትምህርቶች ሳይሆን ጠለቅ ያለውን መንፈሳዊ ነገር ማለትም ጠንካራ ምግብና አጥንትን የምትቆረጥሙበት ጊዜ ሊሆን ይገባ ነበረ ማለቱ ነው፡፡
4. ቁ13ትን አንብበን ወደዚህ አይነቱ ማሰሪያ ሃሳብ መምጣት ትክክል አይደለም፤ ምክንያቱም ቁጥሩ የሚናገረው ኑሮውን በወተት ብቻ ስላደረገና ገና የሚጋት፣ ሰው የሚግተው በተለይም በእንግሊዘኛው “anyone who lives on milk” ስለሚል ሌላ ምግብ መመገብ የማይችልን ሰው ያመለክታል፡፡ 1ኛ ጴጥ 2፡2 እንደ ህጻን እንድንሆንና መንፈሳዊ ወተትን እንድንመኝ ሲያበረታታ፤ ዕብ 5፡13 ደግሞ በሌላ ገጽታው ህጻን ሆኖ መቆየት እንደማይኖርብን ይነግረናል፤ በሌላ በኩል ደግሞ 1ኛ ጴጥ 2፡2 ወተት ብሎ የሚለው የክርስትናን የመጀመሪያ ትምህርት ብቻ ሳይሆን ጠቅላላ የእግዚአብሄርን ቃል የሚል ይመስላል፤ ህጻን የሚለው ሃሳብ ደግሞ በሁለቱ ቦታ የተለያ ሃሳብ ይዞ ይገኛል፡ ዕብራዊያን ባለማደግ ላይ ሲያተኩር፣ በ1ኛ ጴጥ ደግሞ እንደህጻን የመራብንና የመጠማትን ነገር ያሳየናል፡፡
5. ከዚህ ክፍል መንፈሳዊ ጨቅላነትን የሚያመለክቱት ነገሮች፡ ሀ) ለቃሉ ዳተኛ መሆን ቁ11፣ ለ) ለሌሎች ለማካፈል አለመብቃት ቁ12፣ ሐ) ሁልጊዜ እንደህጻን ወተት መጋትና ቁ12-13፣ መ) መልካሙንና ክፉውን መለየት አለመቻል ማለትም ትንቢትን፣ ስብከትን ወይም ደግሞ ከመንፈስ ቅዱስ እንደሆነ አስረግጦ የሚመጣውን መልዕክት ሁሉ ለይቶ መረዳት አለመቻል ቁ14 ናቸው፡፡
6. በ6፤1 ላይ ‹‹ትተን›› የሚለው ሃሳብ አስቀድመን የተማርነውን ነገር መርሳትና መተው ማለት ሳይሆን እዚያ ላይ ሳናበቃ በተመሰረተው መሰረት ላይ እየገነባን ማሳደግ እንደሚገባን ለማስተማር ነው፡፡ በዕብ 3፡14 ላይ ያለው ሃሳብ ከዚህ ጋራ አይቃረንም፤ በ2ኛ ጴጥ 3፡18 ላይ እንደምንመለከተው በክርስቶስ እውቀትና በጸጋ ማደግ ከዚህ ሥጋ እስከምንለይ ድረስ የህይወታችን ግብ ሊሆን ይገባል፡፡
7. ከሞተ ሥራ ንስሃ፣ በእግዚአብሄር ስለማመን፣ ስለ ጥምቀቶች፣ እጆችን ስለመጫን፣ ስለሙታን ትንሳኤና፣ ስለዘላለም ፍርድ የሚሉት ናቸው፡፡ እነዚህን ነገሮች ደጋግመን ማድረግ የማያስፈልገን፤ ስድስቱንም ነገሮች ብንመለከት አንድ ጊዜ ካደረግን ደግመን ማድረግ የማይጠበቅብን ነገሮች ናቸው፡፡
8. እንደ ሰው ውሳኔ ማስተላለፍ እንችላለን፤ ነገር ግን ይህንን ውሳኔ ከግብ ሊደርስ እንዲችል ሊያደርግ የሚችለው እግዚአብሄር ብቻ እንደሆነ ጸሐፊው ሲያረጋግጥ ነው፡፡
9. ችግር የምናየው ከተማሪው ነው፡፡ ችግሩም ለመማር ዳተኛ መሆናቸው ነው፡፡ የተቀረው መልስ በእያንዳንዱ ሰው እንደተሰማው መልስ ይስጥበት፡፡

# <u>ጥናት ዘጠኝ ዕብ 6፡4-20 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ብርሃን በርቶላቸዋል፣ ሰማያዊውን ስጦታ ቀምሰዋል፣ ከመንፈስ ቅዱስ ተካፋይ ሆነዋል፣ የእግዚአብሄርን ቃልና የሚመጣውን ዓለም ሃይል ቀምሰዋል፡፡ እነዚህን ከካዱ ወደንስሃ መመለስ የማይቻለው፡ እነሱ ለገዛ ጥፋታቸው የእግዚአብሄርን ልጅ መልሰው ይሰቅሉታል ያዋርዱታልም፡፡
2. በእኔ አመለካከት እነዚህ ሁለቱ የተለያዩ ዓይነት ሰዎች ናቸው፤ ይህንንም ማለት የሚያስችለኝ ዋነኛ ምክንያት በቁ10 ላይ በተለይም በእንግሊዘኛው (we are confident of better things in your case) እያለ የሚናገረው አነጋገር ግልጽ የሆነ ልዩነትን እንደሚያደርግ እንረዳለን፡፡
3. በቁ7 ላይ የምናያት መሬት 9-12 ውስጥ የሚናገራቸውን ሰዎች ትወክላለች፤ ምክንያቱም መሬቲቱ ዝናብ ጠጥታ መልካም ፍሬ እንደምትሰጥ እነዚህ ሰዎችም የደህንነት በረከትን ተቀብለው ከዚያ ጋራ የተያያዘ ታላቅ ፍሬ እንደሚታይባቸው ይናገራል፡፡ በቁ8 የምናያት ግን ዝናቡን ጠጥታ የምታፈራው እሾህና አሜከላ እንደሆነ፤ በቁ4-6 የተጠቀሱትም ሰዎች ያንን ሁሉ መልካም ነገር ተቀብለው ወደ ከህደት መሄዳቸው ከእርሷ ጋራ ያመሳስላቸዋል፡፡
4. ማቴ 7፡21-23 ላይ የሚታዩት ሰዎች ልክ በዕብ 6፡4-6 ላይ እንዳሉት ሰዎች ብዙ መንፈሳዊ ነገሮች በህይወታቸው ታይቷል፡፡ ማቴ 13፡5-6 አብበው መታየትና ቃሉን በደስታ መቀበላቸው ከጊዜ በኋላ ግን መሞታቸው ከዕብራዊያኑ ጥቅስ ጋራ ያመሳስለዋል፡፡ ሥራ1፡17፣ 25 ደግሞ ይሁዳ ከሃዋርያቱ እንደ አንዱ ተቆጥሯል፣ በራሱ አገልግሎቱን ትቶ እስከሄደ ድረስ በጌታ አገልግሎት ሁሉ ተሳትፏል፤ ይህ ሁሉ በህይወቱ ሆኖ ፍጻሜው አለማማሩ ከነዚህ ሰዎች ጋራ ያመሳስለዋል፡፡ በመጨረሻም 1ኛ ዮሐ 2፡19 በአማኞች መሃል ነበሩ እንጂ አማኞች አለመሆናቸው፣ እስከወጡበት ጊዜ ድረስ ማንም አላመኑም ብሎ አላለም፣ እውነተኛ እውነት እንዳልነበራቸው የተገለጠው በወጡ ጊዜ ብቻ ነበረ፤ እነዚህ ሁሉ ሃሳቦች ሲታዩ ከዕብ 6፡4-6 ጋራ የሚዛመድ ሃሳብ እንዳለው ይመስለኛል፡፡
5. ይህ ከድነታቸው ጋራ ተያያዘ የሚለው በቁ10 ላይ ቅዱሳኑ ለፍቅራቸው መግለጫ እያደረጉ ስላለው ተግባር ነው፡፡ ይህ ድርጊትም የበጎ አድራጎትን ነገር ብቻ ለማከናወን እንዳልሆነና ስለ ስሙ ተብሎ የሆነ ስለሆነ በእግዚአብሄር ፊት ዋጋ አለው፡፡ ይህ ለነዚህ ሰዎች ብቻ ሳይሆን እስራኤልን ከግብጽ ሲያወጣ ጀምሮ ‹‹ያገለግለኝ ዘንድ ህዝቤን ልቀቅ›› ስለሆነ አገልግሎት ደህንነትን ሊከተል ይገባል፡፡ ሰዎቹ እያደረጉ ያሉትን ትጋት እያሳዩና እስከ መጨረሻ ማድረግ እንደሚኖርባቸው ያበረታታቸዋል፡፡
6. የአብርሃም ህይወት መነገር ያስፍለገው በቁ12 ላይ በእምነትና በትዕግሥት የተስፋ ቃሉን እንዲወርሱ ለሰጠው ማበረታቻ የአብርሃም ህይወት ከሁሉ የተሻለ ምሳሌ ሊሆን ስለሚችል ከዚያ አንጻር ነው፡፡
7. ማረጋገጥ የፈለገው ሃሳብ የተስፋ ቃሉ እንደማይለወጥ ሲሆን ይህንንም ማረጋገጥ የፈለገውም ለተስፋ ቃል ወራሾቹ ማለትም ለእኛ ሁሉ ነው፤ ይህ ተስፋ እኛንም ማጠቃለሉን በቁ18 ላይ ማየት ይቻላል፡፡
8. ተስፋውን ለማረጋገጥ የተጠቀመባቸው ሁለት ነገሮች፡- የገባው የተስፋ ቃልና በራሱ የማለው መሃላ ናቸው፡፡
9. እያንዳንዱ የራሱን ሃሳብ ይናገር፡፡

# ጥናት አስር ዕብ 7፡1-25 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. መልከ ጼዴቅ የሳሌም ንጉስ ነው፣ የልዑል እግዚአብሄር ካህን ነው፡፡ በአብርሃምና በዚህ ሰው መሃል የምናየው ግንኙነት፤ አንዱ መልከ ጼዴቅ አብርሃምን መባረኩ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ አብርሃም ለእርሱ አስራት መክፈሉ ናቸው፡፡
2. መልከ ጼዴቅ ማለት ‹‹የጽድቅ ንጉስ››ማለት ሲሆን፣ ‹‹የሳሌም ንጉሥ›› ማለት ደግሞ የሰላም ንጉሥ ማለት ነው፡፡ ይህ መልከ ጼዴቅ አባትና እናት የለውም፣ የትውልድ ሃረግ የለውም፣ ለዘመኑ መጀመሪያ የለውም (መወለድን አያውቅም)፣ ለህይወቱ ፍጻሜ የለውም (ሞትን አያውቅም)፣ ካህን ሆኖ ለዘለዓለም ይኖራል፡፡
3. የእስራኤል ህዝብ ከቀድሞ ጀምሮ ከእግዚአብሄር ባሪያ በተሰጣቸው መመሪያ መሰረት በክህነትም ሆነ በንግሥና የሚያገለግሉ ሰዎች የዘር ግንዳቸው ተቆጥሮ ንጉሥ ከይሁዳ ዘር፣ ካህን ደግሞ ከሌዊ ወገን መሆኑ ግድ ስለነበረ ነው፡፡ የነገሥታቶቻቸውም ሆኑ የካህናቶቻቸው የዘመናቸው መጀመሪያና የህይወታቸውም ፍጻሜ የታወቀ በመሆኑ ይህ እንግዳ አመለካከት እንደሚሆን አያጠራጥርም፡፡
4. መልከ ጼዴቅን ታላቅ ያሰኙት ሁለት ነገሮች፡- አንደኛው ከአብርሃም አሥራትን መቀበሉና (ቁ6)፣ ሌላው ደግሞ አብርሃምን መባረኩ (ቁ7) ናቸው፡፡
5. 7፡1-3 ስለ ካህናችን የሚያስተምሩን፤ የጽድቅም የሰላምም ንጉሥ እርሱ እንደሆነና ሌላ ደግሞ ክህነቱ የዘለዓለም ክህነት እንደሆነ ያሳያል፡፡ 7፡4-10 ያለው ደግሞ ካህናቱና ነገሥታቱ ሁሉ ከአብራኩ ከወጡት ከአብርሃምም የበላይ እንደሆነ ያስገነዝበናል፡፡
6. ሀ) በሌዊ ክህነት ፍጹምነት አልተገኘም፣ ለ) እንደ መልከ ጼዴቅ ባለ ሹመት የሚመጣ ካህን ማስፈለጉ፣ ሐ) የክህነቱ ዓይነት ሲቀየር ህጉም መቀየር እንደሚያስፈልገው እንመለከታን፡፡ ክህነት ሊገኝ የሚችልባቸው ሁለት መንገዶች፡- አንዱ እንደነ አሮን የትውልድን የነገድ ግንድ ጠብቆ ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ እንደ ክርስቶስ የማይጠፋ የህይወት ሃይል የሚሆን ክህነት ናቸው፡፡
7. የቀድሞው ትዕዛዝ ደካማና የማይጠቅም መሆኑ፣ ህጉ ማንንም ፍጹም ሊያደርግ አለመቻሉ፣ ያለ መሃላ መሆኑ፡፡ በዚህ ክፍል መሰረት የካህን ዋነኛ ተግባር በቁ19 ላይ የሰፈረ ሲሆን ይህም እኛን ወደ እግዚአብሄር ለማቅረብ መቻል ነው፡፡
8. ሟች ስለሆነና ሞት ስለከለከለው ነው፡፡ በሁለቱ የክህነት ዓይነቶች መሃል ዋነኛ ልዩነት ሆኖ የቀረበው በትውልድ የሚገኘው ሞት በቋሚነት እንዳያገለግሉ የሚከለክላቸው ሲሆን፤ ኢየሱስ ግን ለዘላለም የሚኖር በመሆኑ ክህነቱ የዘለዓለም ነው፡፡
9. ዘወትር ስለእነርሱ እየማለደ ስለሚኖር ነው፡፡ እንደነዚህ ከመሳሰሉት ክፍሎች ኢየሱስ እየማለደ ስላለበት ምክንያት የምንረዳው፡ ሊያሰናክለንና ሊጥለን የተቻውን ሁሉ ከሚያደርግ ባላጋራ እንድንጠበቅና በሃጥያት ስንገኝ ይቅርታን እንድናገኝ የሚማልድልን መሆኑን ነው፡፡ የተቀሩት ጥያቄዎች እያንዳንዱ ሃሳቡን ይስጥባቸው፡፡

# ጥናት አስራ አንድ ዕብ 7፡26-8፡13 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ያስፈልገናል የሚለው፡- ቅዱስ፣ ነቀፋ የሌለበት፣ ንጹሕ፣ ከሃጥያተኞች የተለየና፣ ከሰማያት በላይ የከበረ ነው፡፡ ለዚህም ምክንያት የሚያቀርበው በቁ27 ላይ እንደ ሌሎቹ ሃጥያት ስለማያውቀው ለራሱ መስዋዕት ማቅረብ አለማስፈለጉ፣ ለሚረዳቸውም ሰዎች ተደጋጋሚ መስዋዕት ሳይሆን አንደና ለመጨረሻ የሚሆን ራሱን መስጠቱ ነው፡፡
2. በዚህ ቁጥር መሰረት እግዚአብሄር ሊቀ ካህናትን ለመሾም የተጠቀመባቸው መንገዶች፡ ህግና መሃላ ናቸው፡፡ በሁለቱ መሃል የምናየው ልዩነት፤ ህግ ደካማ ሰዎችን የሚሾም ሲሆን፣ መሃሳው ደግሞ ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሄር ልጅ ሾሟል፡፡ በተጨማሪ ግን ህግ ብዙዎችን ሲሾም መሃላ ግን አንድ ብቻ ሾመ
3. ዋነኛው ሊያስተላልፍ የፈለገው ሃሳብ፡- በሰማይ ስላለ፣ ስለተቀመጠ፣ በሰው በተተከለ ድንኳን ውስጥ ስለማያገለግል፣ አገልግሎቱ በእውነተኛይቱ ድንኳን ውስጥ ስለሆነና፣ አሁንም እያገለገለ ስላለው የተሻለ ሊቀ ካህናት እንዲረዱ ነው፡፡ ‹‹እንደዚህ ያለ›› የሚለው ቃል የሚጠቁመን በተለይ 7፡26-28 ያለውን ሃሳብ ነው፡፡
4. ሶስቱ የተወዳደሩት ነገሮች፡ ኪዳን፣ አገልግሎትና፣ የተስፋ ቃል ናቸው፡፡ በልጠው የተገኙት ሁሉ የሚጠቁሙት ወደ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፡፡
5. ወረድ ብለን ቁ8ትን ስናነብ ግልጽ ይሆንልናል፡፡ ጉድለት የተነኘው በህዝቡ ላይ እንጂ በህጉ ላይ እንዳልነበረ ማየት ይቻላል፤ ይህንን ሃሳብ ሊያረጋግጥልን እንዲችል ሮሜ 7፡12ትን ማንበብ ይረዳል፡፡
6. እነዚህ አባቶች የተባሉት በሙሴ አማካኝነት ከግብጽ ከባርነት ነጻ ያወጣቸው ናቸው፡፡ በዘጸ 19፡5-6 ላይ የምናነበው ኪዳን የተመሰረተው እግዚአብሄር የራሱን ድርሻ ያደርጋል ህዝቡ ደግሞ ህግጋቱን በመጠበቅ ለእርሱ በመታዘዝ በረከት ያገኛሉ ነው፡፡
7. አዎን ቃሉን ጠብቋል፤ ምክንያቱም እነርሱ ቃሉን ባለመጠበቃቸው እርሱም ይህንን እንደሚያደርግ በዘጸ 24፡4-8 ነገሯቸዋል፡፡ በእነዚህ ቁጥሮች እንደምንመለከተው ቃል ኪዳኑን የገባው ራሱ እግዚአብሄር ብቻውን ነው፡፡
8. በዚያን ዘመን በነበሩ ሰዎችና በእኛ መካከል የጉድለት መገኘትን አስመልክቶ ምንም ልዩነት እንደሌለን ሮሜ ምዕ 1-3ትን ማየት ይቻላል፡፡ ይህንን ኪዳን ከፊተኛው የተሻለ የሚያደርገው በሰዎች ችሎታ ላይ ያልተመሰረተ መሆኑና የቃል ኪዳን መጠበቅ የሚጠበቅበት እግዚአብሄር ብቻ መሆኑ ነው፡፡

## ጥናት አሥራ ሁለት ዕብ 9፡1-14 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በመጀመሪያው ክፍል ውስጥ የሚገኙት ነገሮች፡ መቅረዙ፣ ጠረጴዛውና፣ የመሥዋዕቱ ህብስት ናቸው፡፡ እነዚህ ነገሮች የሚገኙበት ክፍል ቅድስት ተብሎ ይጠራል፡፡
2. ይህ ክፍል ቅድስተ ቅዱሳን ተብሎ ይጠራል፡፡ ይህንን ክፍል ቅድስት ከተባለው ክፍል የሚለየው ነገር መጋረጃ ነበረ፡፡ በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ የሚገኙት ሁለት ነገሮች፡- የወርቅ ማዕጠንትና፣ የኪዳኑ ታቦት ነበሩ፡፡
3. የኪዳኑ ታቦት የያዛቸው ነገሮች፡- የወርቅ መሶብ፣ የአሮን በትርና፣ ኪዳኑ የተጻፈበትን ጽላት ይዟል፡፡ መናው የተቀመጠውም በወርቅ መሶቡ ውስጥ ነበረ፡፡ በታቦቱ ላይ የነበረው የስርየት መክደኛውን የሚጋርዱ የክብር ኪሩቤል ነበሩ፡፡
4. ጸሐፊው ይህንን አስመልክቶ መናገር የሚችለው እጅግ ብዙ ነገር እንዳለውና ጊዜ የማይበቃው እንደሆነ የሚጠቁም አነጋገር ተናግሮ ነው በቁ5 ላይ የጨረሰው፤ ስለዚህ አምስቱ ቁጥርች ላይ ያየነውንና የጸሐፊውን አነጋገር ስናይ የቀድሞው ኪዳን ምን ያህል የተወሳሰበና ለተራው ህዝብ ለመረዳት የሚያስቸግር እንደሆነ ማየት ይቻላል፡፡ ሁለተኛው ኪዳንን በተመለከተ ነገሮች ሁሉ የተካተቱት በክርስቶስ ውስጥ ስለሆነ ለሰው ሁሉ ለመረዳት ቀላል አድርጓልናል፡፡
5. ወደ መጀመሪያው ክፍል የሚገቡት ካህናቱ ሁሉ ሲሆኑ፤ ወደ ውስጠኛው ክፍል ሊገባ የሚችለው ግን ሊቀ ካህናቱ ሲሆን እርሱም በአመት አንድ ጊዜ ብቻ አስፈላጊውን የሃጥያት መስዋዕት ለራሱና ለህዝቡ ሁሉ ለማቅረብ መግባት ይችላል፡፡
6. ወደ እግዚአብሄር መቅረብ እጅግ ከባድ፣ ለሁሉም ሰው የማይሆንና ሥርዓቱም የበዛ፣ እንዲሁም እጅግ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ነገር መሆኑን እናያለን፡፡ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ እነዚህን ሁለት ክፍሎች የሚከፍለው መጋረጃ እስካለ ድረስ ወደ እግዚአብሄር በቀጥታ የሚያደርሰው መንገድ እንዳልተከፈተ እንድናውቅ ይፈልጋል፡፡ ራሳችን ካላቆምነው በስተቀር አሁን የመጀመሪያይቱ ድንኳን ሳይሆን ሁለተኛይቱ ድንኳን ውስጥ ነው አገልግሎት የሚካሄደው፤ ማለትም መጋረጃ የለውም ማለት ነው፡፡
7. አዲሱ ስርዓት የሚለው በቁ11 ላይ መጣ የሚለው ክርስቶስ ያመጣውን አዲስ ኪዳን ማለቱ ነው፡፡
8. በብሉይ ኪዳን የሚካሄደው ሥርዓት ሊያነጻ የሚችለው ውጫዊ መንጻትን ብቻ እንጂ ውስጥ ገብቶ የሰዎችን ህሊና የማንጻት ጉልበት አልነበረውም፡፡ የአዲስ ኪዳኑ መስዋዕት ግን የውስጡን ህሊናችንን የማንጻት ችሎታ ነው ያለው፡፡ ከእግዚአብሄር ጋራ ትክክለኛ የሆነ ግንኙነት እንደሌለንና እርሱን እንደበደልነው ህሊናችን እየወቀሰን በድፍረት አርሱን ለማምለክም ሆነ ለማገልገል አስቸጋሪ ይሆናል፡፡
9. የመጀመሪያይቱ ድንኳን በሰው እጅ የተሰራች ስትሆን ሁለተኛይቱ በሰው እጅ አልተሰራችም፤ የመጀመሪያይቱ ከዚህ ፍጥረት ነች ሁለተኛይቱ አይደለችም፣ የመጀመሪያይቱ በየአመቱ ሊቀ ካህኑ ይገባባታል ሁለተኛይቱ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ገብቶባታል፣ የመጀመሪያይቱ የበግና የኮርማ ደም፣ ሁለተኛይቱ የክርስቶስ ደም…፡፡ በሁለተኛይቱ ድንኳን መጋረጃ አለመኖሩ አምላኬን ለማምለክና ለማገልገል ሰተት ብዬ ለመግባት የሚከለክለኝ ነገር እንደሌለ እረዳለሁ፤ ክርስቶስም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መግባቱ የማይሻር ይቅርታን እንዳስገኘልኝ እረዳለሁ፡፡

# ጥናት አስራ ሶስት ዕብ 9፡15-28 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ ቁጥር መሰረት ክርስቶስ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ የሆነው የተጠሩት እግዚአብሄር ተስፋ የሰጠውን የዘለዓለም ርስት እንዲቀበሉ ነው፡፡ የክርስቶስ ሞት የአዲስ ኪዳንን ብቻ ሳይሆን የብሉይ ኪዳንንም ቅዱሳን እንደሚያድን የሚያሳየን በቁ15 ላይ የምናየው ‹‹በመጀመሪያው ኪዳን ሥር በነበሩበት ጊዜ ከሰሩት ሃጥያት ነጻ ለማውጣት ቤዛ ሆኖ ሞቷልና› የሚለው ሀሳብ ነው፡፡
2. ቁ15 እንደሚነግረን ርስትን ለመቀበል ተስፋ የተሰጣቸው ሰዎች እንዳሉና እነዚህም ሰዎች የተገባላቸውን ርስት ለመውረስ ቃል የገባው ኢየሱስ ከሞተ በኋላ ብቻ በሥራ ላይ መዋል እንደሚችል ሲያስረዳ ነው፡፡
3. ሁለቱ ኪዳኖች የሚለዩት የመጀመሪያው አድርግ ያለበለዚያ ትሞታለህ ከማለት በስተቀር ማድረግ ባይችል ማድረግ እንዲችል የሚያደርገው ምንም የሚረዳው ነገር የለም፤ ሁለተኛው ኪዳን ግን አድርግ ብሎ ያዘዘውን ለመፈጸም የሚያስችለውን ጉልበትና ሃይል ይሆነው ዘንድ እግዚአብሄር ራሱ በውስጡ መንፈሱን ያስቀመጠ ስለሆነ ብቃት ራሱ ሆኖታል፡፡
4. ይህንን ያለበት ምክንያት በብሉይ ኪዳንም እግዚአብሄር ከህዝቡ ጋራ ቃል ኪዳን ሲገባ በዘጸ 24 ላይ እንደምናየው አስፈላጊው ደም ፈሶ መሆኑን ሲገልጥ ነው፡፡
5. ይህችን መቅደስ የሚያስተዋውቃት፤ የእውነተኛይቱ ድንኳን ምሳሌና፣ በሰው እጅ ያልተሰራች በማለት ነው፡፡ ክርስቶስ ወደ ሰማያዊቱ መቅደስ የገባው ስለእኛ በእግዚአብሄር ፊት ለመታየት ነው ይላል፡፡ ለመታየት የሚለው አነጋገር የሚገባኝ በ1ኛ ዮሐ 2፡1 ላይ እንደሚናገረው በእግዚአብሄር ፊት በሁሉም መንገድ በቂ ሆነን እንድንገኝ የሚፈጽመው ሥራ ነው፡፡
6. ቁ9 እና 16 እንደምናየው የክርስቶስ ደም የውጭውን ሰውነት የሚያጸዳ ሳይሆን የሰዎችን ህሊና ማንጻት የሚችል ስለሆነ መደጋገም የሚያስፈልገው ዓይነት መስዋዕት አይደለም፡፡ በተጨማሪም ቁ26 እንደሚነግረን ‹‹ሃጥያትን…ለማስወገድ ተገልጧል›› የሚለው ሃጥያትን የመክደን ሳይሆን የማስወገድ ብቃት ስላለው መደገም አላስፈለገውም፡፡
7. ሰዎች አንድ ጊዜ እንደሚሞቱና ከዚያ በኋላ ደግሞ ለፍርድ እንደሚቀርቡ ሲነግረን ስለክርስቶስ ግን አንድ ጊዜ ስለሰዎች ሃጥያት የሞተ ቢሆንም እንደ ሰዎች ለፍርድ የሚቀርብ ሳይሆን ለመፍረድ ፈራጅ ሆኖ እንደሚመለስ እንገነዘባለን፡፡
8. ለሚጠባበቁት በማለት የተነገረላቸው ሰዎች እንደ እኛ ያሉ ምጻቱን የሚጠባበቁ ሲሆኑ እነዚህ በክርስቶስ ደም ታጠበው ደህንነትን ያገኙ ሰዎች ናቸው፡፡ ይህ በዚህ ክፍለ ያመጣላቸዋል የሚለው ድነት አሁን የለበስነው ሟቹ ሥጋ ሁሉ መዳን የሚያገኝበትና ከማናቸውም ሃጥያት ነጻ የምንሆንበትን ቅድስናችን ሙላት አግኝቶ ፍጹምነት የምናገኝበትን የደህንነታችን ሁሉ መደምደሚያ ማግኘት ማለት ነው፡፡ ሀ) ድነናል(ኤፌ 2፡8 1ቆሮ 15፡2) ለ) እየዳንን ነው(1ኛ ጴጥ 1፡9 2፡2 ፊሊ 2፡12) ሐ) እንድናለን(ዕብ 9፡28 ሮሜ 8፡23) እነዚህ Justification, Sanctification, Glorification የሚባሉት ሃሳቦች ናቸው፡፡
9. እያንዳንዱ የራሱን ሃሳብ ይስጥበት፡፡

# ጥናት አስራ አራት ዕብ 10፡1-18 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ሕጉን የሚያስተዋውቀው ጥላ እንጂ እውነተኛው አካል እንዳልሆነ የተናገረ ሲሆን ወደፊት የሚመጡ ያላቸውን ነገሮች ደግሞ መልካም ነገሮች በማለት ጠርቷል፡፡
2. በየዓመቱ፣ ዘወትር፣ ያለማቋረጥና ተደጋጋሚ የሚሉት ቃላት ናቸው፡፡ ቁ1 እንደሚናገረው በተደጋጋሚ ይቀርብ የነበረው መስዋዕት የህዝቡን ሃጥያት ማስወገድ ያልቻለው ህጉ መጀመሪያውኑ ሲሰጥ እንደዋነኛ ነገር ሳይሆን ሊመጣ ላለው ዋነኛና መልካም ነገር ጥላ ብቻ ስለነበረ ነው፡፡
3. አንደኛው መስዋዕትን በተደጋጋሚ ማቅረብ ይተው ነበረ፣ ሌላው ደግሞ ሰዎቹ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ስለሚነጹ በህሊናቸው ሃጥያተኛነት ባልተሰማቸውም ነበረ የሚሉት ናቸው፡፡
4. እነዚህ በየዓመቱ የሚካሄዱት መስዋዕቶች ሰዎቹን ፍጹም ማድረግ ካለመቻላቸውም አልፈው ሃጥያተኛነታቸውን በየጊዜው ያስታውሷቸዋል፡፡ የአዲስ ኪዳኑ መስዋዕት ግን ለሃጥያት ይቅርታ አንዴ ለመጨረሻ የቀረበ ስለሆነ የሃጥያትን ይቅርታ እንደተቀበልን ዘወትር የሚያስታውሰን ስለሆነ የምስጋና ምክንያት በየጊዘው ይሰጠናል፡፡
5. ያልፈለጋቸው ነገሮች የተባሉት መስዋዕትና መባ ሲሆኑ ደስ ያልተሰኘባቸው ደግሞ የሚቃጠል መስዋዕትና ለሃጢያት የሚቀርብ መስዋዕት ናቸው፡፡ በእነዚህ ነገሮች ደስ ያልተሰኘበት ምክንያትም ሰዎችን ፍጹም ማድረግ ስለማይችሉና ሃጥያትን ማስወገድ የማይችሉ ስለሆነ ነው፡፡
6. ቁ7 ላይ እንደምንመለከተውና በቁ9 ላይም እንደተደገመ የክርስቶስ መምጣት ምክንያት የእግዚአብሄርን ፈቃድ ለመፈጸም ነው፡፡ በምንባቡ መሰረት የእግዚአብሄር ፈቃድ የህዝቡ ፍጹም መሆንና የሃጥያታቸው መወገድ ነበረ፡፡
7. እዚህ ‹‹ፈቃድ›› እያለ የሚናገረው ከላይ በቁ7 እና ቁ9 ላይ ስለተጠቀሰው የእግዚአብሄር ፈቃድ ነው፡፡ ከዚህ አነጋገርም ስለቅድስና መረዳት የምንችለው፤ መቀደሳችን በሰው የታሰበ ነገር ሳይሆን እግዚአብሄር አስቀድሞ የወሰነው ነገር መሆኑንና ይህም ሙሉ በሙሉ ፈቃዱ መሆኑን እንረዳለን፡፡
8. እነዚያ አገልግለው በምድር ይሆናሉ ያኛው በአብ ቀኝ አለ፤ እነዚያ የቆሙ ሲሆን ያኛው ግን ተቀምጧል፣ እነዚያ ለዘለዓለም አንድ ዓይነት መስዋዕትን ያቀርባሉ ያኛው ግን አንድ መስዋዕት ለዘለዓለም አቅርቦ ጨረሷል፡፡
9. በዚህ አንድ መስዋዕት ህዝቡ ሁሉ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በአብ ፊት ፍጹምነትን ተቀብሏል፤ በሌላ በኩል ግን ይህንን በክርስቶስ የተገኘውን በዕለት ዕለት ኑሯችን ከቅድስና ወደ ቅድስና መራመድ እንደሚጠበቅብን የሚጠቁመን ነው፡፡
10. ከነዚህ ክፍሎች መቀደሳችን የእግዚአብሄር ፈቃድ መሆኑን፣ ለመቀደስ ፍላጎትና ጥማት ሊኖረን እንደሚገባ፣ ሁልጊዜ እንደጳውሎስ እንዳልደረስንበት በማመን እጆቻችንን መዘርጋት እንደሚገባን ሲሆን በሌላ በኩል ግን በአብ ፊት ፍጹማን ሆነን እንደምንታይ ማወቅ ይኖርብናል፡፡ የተቀረውን እያንዳንዱ በራሱ ይመልሰው፡፡

## ጥናት አስራ አምስት ዕብ 10፡19-25 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ወደ ቅድስተ ቅዱሳን መግባት ያስቻለን ነገር በመስቀል ላይ የፈሰሰው የክርስቶስ ደም ነው፡፡ ወደዚህ ሥፍራ መግባት ትልቅ ነገር የሆነበት ምክንያት ከእግዚአብሄር ጋራ ግንኙነት እንዲኖር ካስፈለገ እርሱ የሚገኝበት ሥፍራ ይህ በመሆኑ ወደዚያ ሥፍራ የመግባት ነገር ወሳኝ ስለሆነ ነው፡፡ ድፍረት አግኝተናል ማለቱ ከሊቀ ካህናቱ በስተቀር እርሱም በአመት አንድ ጊዜ ብቻ መግባት የሚችል ሲሆን ማንም ከዚህ ውጭ መግባት ቢሞክር ሟች በመሆኑ ሲሆን፤ ዛሬ ግን በደሙ ድፍረት ተገኝቷል፡፡
2. በነዚህ ቁጥሮች እንድናደርግ የተጠየቅነው አንድ ነገር ቢኖር ወደ እግዚአብሄር እንድንቀርብ ነው፡፡ ጸሃፊው በድፍረት ይህንን ማለት የቻለው ቁ21 እንደሚናገረው በእግዚአብሄር ቤት ላይ አለቃ የሆነ ሊቀ ካህን ስላለን ነው፡፡ ወደ እግዚአብሄር ስንቀርብም፡ ልባችንን ተረጭተን፣ ሰውነታችንን በንጹህ ውሃ ታጥበን፣ በእውነተኛ ልብ እና በሙሉ እምነት ልንቀርብ ይገባናል፡፡ ዘሌ 8፡6ትን አንብብ ፡፡
3. በቁ23 የተጠየቅነው ተስፋውን አጥብቀን እንድንይዝ ነው፡፡ ተስፋው በመጀመሪያ ደረጃ ያመነው ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ የምንናገርለት/የምንመሰክረው ነው፡፡ ተስፋውን አጥብቀን መያዝ ያለብን ምክንያት፤ ተስፋን የሰጠው እግዚአብሄር ታማኝ ስለሆነ ነው፡፡
4. እርስ በእርሳችን እንዴት እንደምንነቃቃ እናስብ፣ መሰብሰባችንን አንተው፣እርስ በእርሳችን እንበረታታ፡፡ ሐዋ ሥራ ላይ የቤተ ክርስትያን ሽማግሌዎች መንጋውን እንዲጠብቁ ቢናገርም፤ በኤፌሶን ላይ ደግሞ ቅዱሳንን ለአገልግሎት ማዘጋጀት የሚለው ሃሳብ በዕብራዊያን 10፡24 ላይ ያየነውን ዓይነት አገልግሎት እርስ በእርሳቸው መገላገል እንዲችሉ የሚበቁበት ደረጃ ላይ የማድረስ ሃላፊነት ይጠበቅባቸዋል፡፡
5. የመነቃቃቱና የመበረታታቱ ግብ ሁላችን ዕለት በእለት ፍቅራችን እየጋለ እንዲሄድና መልካም ሥራን ለመስራት ዝግጁነታችን እንዲጨምር ነው፡፡ በቁ24 ላይ ‹‹እናስብ›› የሚለው ቃል እግረ መንገድ የሚደረግ እንዳልሆነ፣ ትዝ ሲለን የሚደረግ እንዳልሆነ፣ ነገር ግን ጊዜ ሰጥተን፣ ቁምነገር ብለን፣ በጸሎት እግዚአብሄርን ጠይቀን ማድረግ የሚኖርብን ነገር እንደሆነ እገነዘባለሁ፡፡
6. እንዳናደርገው የታዘዝነው አንድ ነገር ከቅዱሳን ጋራ መሰብሰባችንን እንዳንተው ነው፡፡ ሰዎች መሰብሰብን ሊተው ከሚችሉባቸው ምክንያቶች መሃል፡ የሥራ ብዛት፣ የስፍራ ርቀት፣ ከቅዱሳን ጋራ ባላቸው አለመግባባት፣ ጥቅሙን አለመረዳትና የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡
7. በቁ25 ላይ ስብሰባ የሚለው እርስ በእርሳችን ስለሚል እሁድ ስብከት የምንሰማበትን ሳይሆን፤ ማናቸውም ቅዱሳን ተሰባስበው የሚነቃቁበትና የሚበረታቱበት ስብሰባ እንደሆነ እገምታለሁ፡፡ ስከቅዱሳን ጋራ የመሰብሰባችን አስፈላጊነት በተለይ የጌታ መምጫ እየተቃረበ መምጣቱ ግልጽ ሆኖ ስታይ አብዝተን ልናደርገው እንደሚገባን ይነግረናል፡፡ ማቴ 24፡12 ‹‹ከፋት ስለሚገን የብዙዎች ፍቅር ይቀዘቅዛል›› እዚህ ውስጥ የምናያቸው ሁለት ነገሮች ማለትም የከፋት መግነንና የፍቅር መቀዝቀዝ የተባሉት በዕብ 10፡24 ላይ የስብሰባችን ዋነኛ ምክንያቶች ሆነው የተጠቀሱት መልካም ሥራናለ፣ ፍቅር ናቸው፡፡
8. ለከፋት መግነንና ለፍቅር መቀዝቀዝ መፍትሄ አድርጎ የሰጠን ነገር ከቅዱሳን ጋራ ሳያሰልሱ መሰብሰብን ሲሆን፤ የስብሰባችንም ዓላማ ለመልካም ሥራና ለፍቅር ህይወት እርስ በእርስ መበረታታት ነው፡፡

## ጥናት አስራ ስድስት ዕብ 10፡26-39 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ዕብ 10፡19-25 ያለው ክፍል በእግዚአብሄር ጸጋና ፍቅር ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ የዛሬው ምንባብ ደግሞ በእግዚአብሄር ሌላኛው ባህርይ ማለትም በቅድስናው ላይ ያተኮረ ነው፤ ይህም የእርሱ ባህርይ ፍቅር ብቻ ያለመሆኑንና ቅዱስናውን የማያመቻምች አምላክ በመሆኑ ሃጥያትን ማስተናገድ ስለማይችል በሃጥያት ላይ ውሎ አድሮም ቢሆን ሳይፈርድ እንደማይቀር ያስተምረናል።
2. በእነዚህ ሁለት ክፍሎች ማስጠንቀቂያ የሚሰጣቸው ሰዎች የተለያዩ እንደሆኑ አያለሁ፤ ምክንያቱም በዕብ 6፡4-6 ላይ በሶስተኛ ሰው ማለትም እነርሱ እያለ የሚናገር ስለሆነ እንደ እርሱ ያሉትን የማይጠቀልል እንደሆነ የምረዳ ሲሆን በአንጻሩ ደግሞ በ10፡26 ላይ ራሱንም ጨምሮ በአንደኛ ሰው እኛ እያለ ስለሚናገር አማኞችን እንደሚናገር አያለሁ።
3. ሆን ብሎ በሃጥያት ጸንቶ መመላለስን ጸሃፊው ያየበት በሶስት ዓይነት ሲሆን እነርሱም፡ የእግዚአብሄርን ልጅ እንደመርገጥ፣ የኪዳኑን ደም እንደ ተራ ነገር መቁጠርና፣ የጸጋውን መንፈስ ማክፋፋት ናቸው። የሙሴን ህግ የናቀ ተመስክሮበት በሞት ይቀጣ ነበረ፤ በአዲስ ኪዳን ሆን ብሎ ኢየሱስን የናቀ ግን ምስክር መጥራትም አስፈላጊ አይደለም ምክንያቱም ፈራጁ ራሱ ኢየሱስ ነው። ቅጣቱም ከሞት የበለጠ እንደሚሆን ክፍሉ ይጠቁመናል።
4. ይህ ‹‹እግዚአብሄር በህዝቡ ላይ ይፈርዳል›› የሚለው ሃሳብ ጸሃፊው እየተናገረ ያለው ህዝቤ ለሆኑ ሰዎች መሆኑን እንረዳለን። እነዚህ በቁ 30-31 ላይ የምናነባቸው ሃሳቦች ብዙ ሰዎች ስለ እግዚአብሄር በአዕምሯቸው ውስጥ ከሳሉት ስዕል በጭራሽ የተለየ ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሄር ለብዙ ሰዎች ፍቅርና ምህረትን የተሞላ አምላክ ብቻ ሲሆን ይህ ክፍል ግን ሌላውን ገጽታውን ማለትም ቅድስናውንና በሃጥያት ላይ የሚፈርድ አስፈሪ አምላክ መሆኑን ያሳየናል።
5. ጸሃፊው በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ አንባቢዎቹን ቀድሞ ወዳሳለፉት ህይወት መለስ ብለው እንዲያስቡ ነው የሚረዳቸው። እያስታወሳቸው ያሉት ነገሮች፡ በመከራ ውስጥ በብርቱ ተጋድሎ መጽናታቸውን፣ በአደባባይ ለስድብና ለስደት መጋለጣቸውን፣ ለስድብና ለስደት ከተጋለጡት ጋራ አብረው በመቆም መከራ መቀበላቸውን፣ ለታሰሩት መራራታቸውንና የንብረታቸውን መዘረፍም በደስታ መቀበላቸውን ሁሉ ያስታውሳቸዋል።
6. የተሸለና ለዘወትር የሚኖር ሃብት እንዳለን ስንረዳ ስለ ምድራዊ ሃብትና ንብረት ያለን አመለካከት ይቀየራል። እነዚህ ሰዎች ምድራዊ ሃብታቸውን ራሳቸው ወደው ለሌሎች በማካፈልም ሆነ ንብረታቸውንም ሲወርሱባቸው የቁሳቁስ ምንነት ስለገባቸው የተቀበሉት በደስታ ነበረ።
7. ሰዎቹ የኖሩትን የእምነት ኑሮ ወይም በእግዚአብሄር ላይ የመታመንን ህይወት ይለዋል። የሚያበረታታበት ሃሳብ መታመናቸው ታላቅ ዋጋ እንዳለው በመንገር ነው።
8. መልካም ጅማሬአቸውን ለመጣል እየተንገታገቱ ላሉት እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች መታገስና መጽናት እንዲችሉ የጌታ መምጣት በደጅ እንደሆነ ማወቃቸው ትልቅ የመበተታቻ ተስፋቸው በመሆኑ ነው።
9. ጸጋውን በማድነቅ ፊሊ 2፡12 እንደሚናገረው ደህንነታችንን በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ ልንይዘው የሚገባን ክቡር ነገር እንደሆነ መረዳት ያስፈልገናል፤ ስለዚህም በብዙ ምስጋና ያፈቀረንን እግዚአብሄርን ልናመሰግነው ይገባናል።

# ጥናት አስራ ሰባት ዕብ 11፡1-12 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እምነት የሚያገለግልባቸው ሁለቱ መስኮች፤ የመጀመሪያው ተስፋ ያደረግነው ነገር እንደሚፈጸም እርግጠኛ የምንሆንበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የማናየው ነገር እውን መሆኑን የምንረዳበት ነገር ነው፡፡ ከዚህ ክፍል በእምነትና በተስፋ መሃል ስላለው ግንኙነት የማየው፤ እምነት የሚመሰረተው በተስፋ ላይ እንደሆነና እምነት እንዲኖር የተስፋ ቃል መኖሩ ግድ እንደሆነ አያለሁ፡፡
2. የሃላፊን ጊዜ በተመለከተ የጌታ የሱስን በመስቀል መሞት ማናችንም ባናይም እንኳን እግዚአብሄር በቃሉ ስለተናገረና ስለማይዋሽ አምነነዋል፡፡ የመጪውን ጊዜ በተመለከተ ደግሞ አሁንም የጌታችንን ምጽአት በተስፋ የምንጠባበቀው እግዚአብሄር በቃሉ ተስፋ ስለሰጠንና እንደማይዋሽ ስለምናውቅ በእምነት እንጠብቀዋለን፡፡
3. በቁ 2 ላይ ‹‹አባቶች›› በማለት የሚናገርላቸው በምዕራፍ 11 ውስጥ የዘረዘራቸውና በተጨማሪም በቁ32 ላይ ‹‹እንዳልተርክ ጊዜ የለም›› ያላቸውን የእምነት ጀግኖች ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ እግዚአብሄር ለአቤል የመሰከረለት በእምነት እንደጸደቀ ሲሆን፤ የአቤልን መስዋዕት ከቃየል የለየው አንድ ነገር እምነት እንደሆነ እናነባለን፡፡
4. እግዚአብሄር በሄኖክ ደስ የተሰኘው በእምነት የሚመላለስ ሰው እንደነበረ በዚያው ክፍል በመቀጠል ከተናገረው ሃሳብ ማየት ይቻላል፡፡ እግዚአብሄርን ለእምነት እጅግ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነገር እንደሆነና አገልግሎታችንም ሆነ ኑሯችን ሁሉ በእምነት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ይጠብቅብናል፡፡
5. የኖህ ሁኔታ የሚያንጸባርቀው፤ የማናየውን ነገር እውን መሆኑን መረዳቱ ነው፡፡ ማለትም እግዚአብሄር ወደፊት ይሆናል ብሎ የተናገረውን ነገር እንደሚሆን አምኖ ተቀብሎ እርምጃ ወሰደ፡፡ ዓለምን መኮነን የሚለው ሃሳብ ደግሞ እግዚአብሄር እውነትን የሚናገር ነው፣ አይዋሽም ስለዚህም ጎርፍ ይመጣል የሚል ስብከት ብቻ ሳይሆን መርከብ በመስራት እግዚአብሄርን እንደሚያምን ማሳየቱ፤ እነርሱ በአንጻሩ ይህ ሊሆን የማይችል ነው በማለት ሃጥያት መስራታቸው ብቻ ሳይሆን አለማመናቸው ለመኮነን ያበቃቸዋል፡፡ እኛም በቃል የምንናገረው ብቻ ሳይሆን በተግባር የምንኖረው ኑሮ የሰዎችን ሃጥያተኛነት መግለጥ እንችላለን ማለት ይቻላል፡፡
6. አብርሃም በእምነት ሲታዘዝ ጥሪ እንደነበረው እናያለን፣ የሚሄድበትን ቦታ አያውቅም ነበረ፣ ኑሮው እንደ መጻተኛ ነበረ፣ የኖረው በድንኳን ውስጥ ነበረ፡፡ የዚህ ዓይነት ኑሮን ለመኖር የወሰነበት ምክንያት መሰረት ያላትን እግዚአብሄር የፈጠራትን ከተማ ይጠባበቅ ስለነበረ ነው፡፡ የሚጠባበቀው አዲስ ከተማ መኖሩ ይህንን ያረጋግጥልናል፡፡
7. አብርሃምን የልጅ አባት ለመሆን ያበቃው ነገር፤ ተስፋን የሰጠውን ታማኝ አድርጎ ስለቆጠረ ነው፡፡ ስለ አብርሃም እርጅና ሲናገር በእድሜ እንደገፋና እንደሞተ ሰው የሚቆጠር ይለዋል፡፡
8. አምናለሁ ካልን እምነታችንን የምናሳርፍበት ጽኑና አስተማማኝ ተስፋ (ዕብ 6፡19) በማለት የሚናገረው አይነት ተስፋ ያስፈልገናል፡፡ ቲቶ 1፡1-2ትን ስናነብ የሚያረጋግጥልን እምነታችን ምንጊዜም ቢሆን ማረፍ የሚኖርበት እግዚአብሄር በሚሰጠው ተስፋ ላይ መሆኑን ነው፡፡

## ጥናት አስራ ስምንት ዕብ 11፡13-29 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እነዚህ ሁሉ በማለት ቁ13 የሚናገረው ስለ አብርሃም፣ ይስሃቅ፣ ያዕቆብና ሳራ ነው፡፡ እነ ሄኖክ፣ ኖህና አቤል ምንም እንኳን አምነው ቢሞቱም በዚህ አነጋገር ውስጥ አይጠቃለሉም፤ ምክንያቱም እነዚህ ሁሉ የተስፋው ቃል ከመሰጠቱ በፊት የነበሩ ሰዎች በመሆናቸው ነው፡፡
2. በዮሐ 8፡56 ላይ አብርሃም ምንም እንኳን በኢየሱስ ዘመን ባይኖርም በእምነት አይኑ እንደተመለከተና በዚያም ደስ እንደተሰኘ ያሳየናል፤ ይህ የሚያሳየን የእምነት ሰዎች የሆኑት ሁሉ በእምነት ሊያዩ የሚችሉት ነገር እንዳለ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች የተገነዘቡት ትልቅ እውነት ይህች የሚኖሩባት ምድር የእነርሱ የዘላለም ማረፊያ እንዳልሆነች ተገንዝበው፤ ኑሯቸውን ይኖሩ የነበሩት እንደ መጻተኛና እንግዳ ነበረ፤ እኛም በ1ኛ ጴጥ 2፡11 ላይ እንደሚያስገነዝበን አኗኗራችን እንደ እነርሱ መጻተኞችና እንግዶች መሆናችንን ተገንዝበን እንድንኖር ነው፡፡
3. የመጻተኛነትና የእንግድነት ኑሮ መኖራቸው የሚያረጋግጠው ነገር ቁ14 እንደሚናገረው ሌላ የራሳቸው የሆነ ሃገር እንዳላቸው ያረጋግጣል፡፡ ‹‹የመመለስ ዕድል ነበራቸው›› ሲል እግዚአብሄር የሰጣቸውን የተስፋ ቃል የመጣልና ወደኋላ የመመለስ ዕድል ነበራቸው ማለት ሲሆን እነርሱ ግን ቁ13 እንደሚነግረን እምነታቸውን እንደጠበቁ መሞታቸውን ያጋግጥልናል፡፡ በዚህ አነጋገሩ ለእነዚህ ወደ ኋላ ለማለት በመቃጣት ላይ ላሉ እብራውያን አንባቢዎች እናንተም መመለስ መብታችሁ ነው፤ ነገር ግን እነርሱ እንደጸኑት ብትጸኑ የተሻለ ኪዳን፣ የተሻለ ሊቀካህን፣ የተሻለ አገልግሎትና የተሻለ ሃገር አላችሁ የሚል መልዕክት ያስተላልፋል፡፡
4. በነዚህ ቁጥሮች መሰረት እግዚአብሄር አምላካቸው ተብሎ ሊጠራ ያላፈረበት ዋነኛ ምክንያት በአንድ አረፍተ ነገር ለመናገር፤ እምነታቸውን እስከ መጨረሻው ሳይጥሉ የራሳቸው የሆነውን ሃገር እየናፈቁ እንደ መጻተኛና እንግዳ ሰው በመኖራቸው ነው፡፡
5. እነዚህ ሁለት ጥቅሶች የሚጋጩ አይደሉም፡፡ በያዕቆብ ላይ ያለው ሰውን ፈትኖ ለመጣል ለሃጥያት የማጋለጥን ሃሳብ የሚናገር ሲሆን፤ ዕብራዊያን የሚናገረው ግን ሰውን ፈትኖ እንደ ወርቅ ለማንጠር የሚደረግ በተፈታኙ መልካም ባህርይ ለማውጣት የሚደረግ ተግባር ነው፡፡ አብርሃም እስማኤልን ሳይሆን የተስፋ ቃል የተቀበለውን እንዲሰዋ ተጠይቆ ፈቃደኛ መሆኑ፤ እግዚአብሄር ከፈለገ ከሙታን ማስነሳት እንደሚችል ማመኑ ይደነቃል፡፡
6. የይስሃቅና የያዕቆብ ድርጊት ከላዩ ሲታይ የእምነት ድርጊት ሆኖ ለማየት ያስቸግራል፤ ሆኖም እነዚህ ሰዎች ልጆቻቸውን ሲባርኩ እግዚአብሄር ይህንን በላያቸው የተናገርኩትን በረከት ያደርገዋል የሚል ጽኑ እምነት በእርሱ ላይ ስለነበራቸው ትልቅ ቦታ ሰጥቷቸዋል፡፡ ዮሴፍ ደግሞ ስለ ዓጽሙ ትዕዛዝ ሲሰጥ እግዚአብሄር ህዝቡን ከግብጽ እንደሚያወጣቸው ሙሉ እምነት እንደነበረው ያረጋግጣል፡፡
7. በእምነት የተከናወኑት ነገሮች፡ ቁ24 ‹‹በእምነት እንቢ አለ››፣ ቁ27 ‹‹በእምነት ወጣ››፣ ቁ28 ‹‹በእምነት አደረገ›› ቁ29 ‹‹በእምነት ተሻገሩ›› የሚሉት ናቸው፡፡ በመጀመሪያውና በመጨረሻው መሃል ቢያንስ የ50 አመታት ልዩነት ይኖራል፡፡ የሙሴ በገጠመኞቹ ሁሉ በእምነት መመላለስ እኛም እምነትን አንድ ቀን የምንለማመደው ነገር ብቻ ሳይሆን ዕብ 11፡13 ላይም እንደምናየው በህይወታችን ዘመን ሁሉ ኖረን የምንሞትበት ነገር እንደሆነ ያስተምረናል፡፡
8. ሙሴ እንደ መጻተኛና እንግዳ ኖሯል የሚያሰኘው በዚህ ዓለም ሊያገኝ የሚችለውን ኮተት ሁሉ ትቶ ከህዝቡ ጋራ ስደትን መምረጡና ክብር ዝና ሊያስገኝለት የሚችለውን የፈርዖን የልጅ ልጅ ላለመባል መምረጡ ሌላ የተሸለ ነገር እንደሚጠብቀው ያረጋግጣል፡፡
9. እያንዳንዱ የራሱን መልስና ሃሳብ ይስጥበት፡፡

## ጥናት አስራ ዘጠኝ ዕብ 11፡29-40 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በቁ29-30 ላይ እምነትን ሲለማመን የምናየው የእስራኤል ህዝብ ነው፡፡ የእስራኤል መሻገርና ለግብጽ የመስጠም ምክንያት የሆነው ነገር የተስፋ ቃልን የመቀበልና ተስፋውን የማመን ጉዳይ ነው እላለሁ፡፡ ዘጸ 14፡15-16ትን ስናነግ እስራኤላውያን ይሻገራሉ እንጂ ግብጽን የሚጠቀልል ነገር የለም፡፡
2. ይህ አነጋገሩ ኤልያስ ከበዓል ነብያት ጋራ የተወዳደረው በእምነት ነበረ፣ ኤልሳዕ ለምጻሙን ንዕማንን ያነጻው በእምነት ነበረ፣ ናታን የዳዊትን ሥልጣን ሳይፈራ የተናገረው በእምነት ነበረ…ወዘተ.
3. እነዚህ ሁለት ዓይነት ሰዎች፤ የመጀመሪያዎቹ በእምነታቸው ምክንያት የተከናወነላቸው ሲሆኑ ሌላዎቹ ደግሞ በእምነታቸው ምክንያት በአስከፊ ነገሮች ውስጥ እያለፉ እምነታቸውን የጠበቁ ሰዎች ናቸው፡፡ ‹‹ከዚህም ነጻ ለመውጣት አልፈለጉም የሚለው አነጋገር ያስገርመል፡፡ ለተቀጣዩ ጥያቄ እያንዳንዱ የራሱን መልስ ይስጥበት፡፡
4. የገጠማቸው ሁኔታ ሞት ሲሆን የመጀመሪያዎቹ የሞቱት እንደ አልአዛር ከሞት ሲነሱ፤ ሌሎቹ የእምነት ሰዎች ደግሞ በዚህ ህይወት እንዲነሱ ሳያደርግ ሁኔታውን በደስታና በፈቃደኛነት እንዲቀበሉት ጸጋን ሲያበዛለቸው ይታያል፡፡ ከዚህ የምማረው እግዚአብሄር ልጆቹን እምነት የሚያለማምድባቸው መንገዶች የተለያዩ ሊሆኑ እንደሚችሉና እርሱ በፈቀደው መንገድ የሚሰራ አምላክ እንደሆነ ነው፡፡
5. እነዚህ ሰዎች እንዲማሩ የፈለገው ማዕከላዊ ሃሳብ የእምነት ሰው በምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ቢያልፍ መንሸራተትና ወደኋላ ማለት እንደማይኖርበት፤ በተለይም በመከራ ውስጥ ማለፋቸው እምነታቸውን ሊያስጥላቸው እንደማይገባ የብዙ ቅዱሳንን ህይወት እንደምስክርነት ለማበረታቻ አስፍሮላቸዋል፡፡
6. ‹‹እነዚህ›› የተባሉት በምዕራፉ ውስጥ ሁሉ የተዘረዘሩትን የሚያጠቃልል ሲሆን መስካሪውም እግዚአብሄር እንደሆነ ከቁ4 ማየት ይቻላል፡፡ እንደ ሰው ቢሆን የእምነት ሰዎች የሚባሉት የአንበሳን አፍ የዘጉት፣ የእሳትን ሃይል ያጠፉት፣ ከሰይፍ ስለት ያመለጡት፣ በጦርነት ድል ያደረጉትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ከዚህ ተነስተን እግዚአብሄር እምነትን የሚመለከትበትና ሰው የሚያይበት መንገድ የተራራቀ መሆኑን እንረዳለን፡፡
7. ጌዴዎን ፈሪ የነበረ ሰው ነበረ፣ መሳ 6፤ ባርቅንም ስንመለከት በእርሱም የምናየው ፍርሃትን ነው መሳ 4፡8፤ ሳምሶንን ደግሞ ስናይ ህይወቱን እንደሞኝ ባለማስተዋል የሚመላለስ ሰው ነበረ፡፡ አብርሃምን ስንመለከት ለሃያ አምስት ዓመታት ልጅ መጠበቁን፣ ልጁን ለመሰዋት እሺ ማለቱንና ዳዊት ደግሞ በትልቅ ትዕግሥትና በእምነት ቃል የተገባለትን ዙፋን መጠበቁን ስናይ የእነ ጌዴዎን ህይወት ብዙዎቻችንን ይወክላል ማለት ይቀላል፡፡
8. በተለያየ ድካም ህይወታቸው የተሞላውን እነዚህን ዓይነት ሰዎች ለአገልግሎቱ መጠቀም የቻለና የእምነት ሰዎች ብሎ የመሰከረ እግዚአብሄር እኔንም ከነድካሜ ሊጠቀምብኝ እንደሚችል እረዳለሁ፡፡ የተቀረው ጥያቄ እያንዳንዱ ሃሳብ በመስጠት ይወያይበት፡፡

# <u>ጥናት ሃያ ዕብ 12፡1-17 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ምስክሮች ማለቱ፤ አንደኛው እነዚህ ሰዎች በራሳቸው ህይወት የተለማመዱት ነገር እንደሆነና በእምነት ማለፍ እንደቻሉ መመስከር ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ እኛን በሩጫው ሜዳ ስንሮጥ እንዳዩን ምስክሮች ይሆናሉ ማለት ይሆናል፡፡ እነዚህ አባቶች በተለያዩ ፈተናዎች ውስጥ በእምነት እንዳሸነፉና በዚያም ሁሉ እግዚአብሄር ታማኝ እንደነበረ ይመሰክራሉ ማለት ነው፡፡
2. በአንድ ቃል መናገር ቢያስፈልግ ‹‹እንፉጥ›› ማለት ይቻላል፡፡ ለሩጫ እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮች፡ ሸክም የሚሆንብኑ ነገሮች ሁሉና፣ ተብትቦ የሚይዘን ሃጥያት የተባሉት ናቸው፡፡ ማንኛውም ስፖርተኛ ማሸነፍ ከፈለገ ሊጥል ወይም ሊተው የሚገባቸው የተለያዩ የምግብ አይነቶች፣ የመጠጥ አይነቶች፣ የሚለብሳቸው ልብሶች፣ የሚተኛበት ሰዓት፣ የሚያዘወትራቸው ነገሮችና የመሳሰሉት ሁሉ ከድል የሚያስቀሩት ከሆነ መተው ወይም መለወጥ ይገደዳል፡፡ የሚተዋቸው ነገሮች ሁሉ መጥፎ ስለሆኑ ሳይሆን ነገር ግን ለማሸነፍ የማይረዱት ወይም ሸክም የሚሆኑበት ነገሮች ስለሆኑ ነው፡፡
3. በህይወታቸው እንዳይከሰት የፈራው ነገር እንዳይዝሉና ተስፋ እንዳይቆርጡ ነው፡፡ ወደዚህ ሁኔታ ሊያመጣቸው ይችላል ብሎ የፈራው ነገር እያለፉበት ያለው ስደት ነው፡፡ ለዚህም መፍትሄ ይሆናል ብሎ የሚነግራቸው ነገር ኢየሱስ ከሃጥያተኞች የደረሰበትን ተቃውሞ እንዲያስቡ ነው፡፡
4. ይህ የደረሰባቸው በቁ3 ላይ በኢየሱስ ላይ ያመጡበት ሰዎች አይነት ማለትም ሃጥያተኞች እያለ የሚጠራቸው ናቸው፡፡ በተለይ ቁ5-11 ላይ የሚናየው ምንም እንኳን ሃጥያተኞች ያድርሱበት እንጂ እግዚአብሄር ከበስተ ኋላቸው መልካሙን ስራውን እየሰራ እንደነበረ ነው የሚናገራቸው፡፡
5. የመጀመሪያው ማነጻጸሪያ ምድራዊ አባቶቻችንን እናከብራቸው ነበረ፤ ለመናፍስት አባት አብልጠን ማክበር ብቻ ሳይሆን መገዛት እንደሚኖርብን ይናገራል፡፡ ሌላው ደግሞ አባቶቻችን መልካም መስሎ እንደታያቸው ይቀጡን ነበረ፤ እግዚአብሄር ግን የቅድስናው ተካፋዮች እንድንሆን ለእኛ ጥቅም ይቀጣናል፡፡ እነዚህ ‹‹በወቅቱ››እና ‹‹በኋላ ግን›› የሚሉት ሁለት ቃላት ቅጣት ጊዜያዊ እንደሆነና ውጤቱ ግን ዘላቂ ወይም ዘላለማዊ እንደሆነ ይነግሩናል፡፡
6. ረሃብ የአሁን ብቻ ሲሆን ብኩርናው ግን ህይወት ዘመኑ ሁሉ የሚሆን ቢሆንም አሳዛኙ ነገር የጊዜውን መምረጡ ነው፡፡ እኛም በዛሬው ነገር የዘለዓለሙን እንዳንለውጥ ሊነግረን ፈልጎ ነው፡፡
7. አንዱ ቅድስና ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ የጽድቅና የሰላም ፍሬ ናቸው፡፡ በሰላም ለመኖር የሚቻለንን እንድናደርግና፣ ለመቀደስ እንድንፈልግ ነው የታዘዝነው፡፡
8. በህይወታችን እየሰራ ያለው ቅድስናን፣ እንዲሁም የጽድቅና የሰላም ፍሬ ለማውጣት ሲሆን እኛንም ያዘዘን እነዚሁኑ ሁለቱን እንድንፈልግ ነው፡፡ ይህ የሚያስተምረኝ እርሱ በህይወታችን የሚሰራውን በአኗኗራችን እንድንገልጠው እንጂ ከራሳችን እነዚህን ነገሮች እንድናመጣ እንደማይጠብቅብን እማራለሁ፡፡
9. ኤሳው ጊዜያዊ ረሃብን መታገስና ብኩርናውን መጠበቅ አልቻም፤ ኢየሱስ ግን የመስቀሉን ሞት ታግሶ ከፊቱ ያለውን ደስታ ያም የእኛን ሁሉ መዳን አስገኘ፡፡ ሰዎች እንደ ዔሳው የዘላለሙን ነገር ለጊዜያዊ ነገር የሚጥሉት በጊዜው ችግራቸው ሊቋቋሙት ከሚችሉት በላይ ሆኖ ስለሚታያቸው ይመስለኛል፡፡ 1ኛ ቆሮ10፡13 ለዚህ ሃሳብ የተሸለ ማብራሪያን ይሰጠናል፡፡

# ጥናት ሃያ አንድ ዕብ 12፡18-29 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. የመጀመሪያዎቹ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ ሲገኙ ሌላዎቹ ግን በደስታ የተሰበሰቡ ይላቸዋል፡፡ እግዚአብሄር፣ መላዕክት፣ በኩራት፣ የጻድቃን መንፈሶች፣ ኢየሱሰ፣ አቤል ተዘርዝረዋል፡፣
2. የአቤል ደም የሚናገረው በዘፍ 4፡10 እንደምናነበው ወንድሙ ቃየል እንደገደለው ስለራሱ ህይወት ነው የሚጮኸው፡፡ የኢየሱስ ደም ደግሞ ደም ሳይፈስ ስርየት የለምና(ዕብ 9፡22) ይኸው ደሜን አፍስሼላችኋለሁ በነጻ ይቅርታን ተቀበሉ ይላል፡፡ በአቤልና በኢየሱስ ደም መካከል ያለው ልዩነት የአቤል ደም ስለራሱ ሲናገር የኢየሱስ ደም ደግሞ ስለሌሎች መዳን ስለሚናገር በዚህ የተሻለ ነው፡፡
3. ተናጋሪ ሆኖ የቀረበው በቁ24 ላይ በደሙ የሃጥያት ስርየት እንዳለ የሚናገረው ኢየሱስ ነው፤ ለዚህም በዕብ 2፡1-3 የምናነበው ሃሳብ በተጨማሪ እግዚአብሄር በመጨረሻው ዘመን ለእኛ የተናገረበት እርሱ እንደሆነና እርሱን አለመስማት ትልቅ ችግር ውስጥ እንደሚጥለን ያረጋግጥልናል፡፡
4. በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በተደጋጋሚ የተጠቀመበት ቃል ‹‹መናወጥ›› የሚለው ሲሆን፤ ይህ ቃል በሶስቱ ቁጥሮች ውስጥ ብቻ አምስት ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ ከዚህም ልንረዳ የፈለገው ሃሳብ እንደ እስራኤል ህዝብ የሚናወጥና የሚጠፋ ርስት ሳይሆን የማይናወጥ የዘላለም ርስት እንዳለን ሊያረጋግጥልን ነው፡፡
5. የማይናወጥ መንግሥት መቀበላችን በውስጣችን የምስጋናን ስሜት ሊፈጥር ይገባል፡፡ ከምሥጋና በተጨማሪ ይህንን ላደረገው አምላክ ተገቢ የሆነ አምልኮ ልናቀርብለት ይገባናል፡፡
6. እግዚአብሄርን በድፍረት እንድንቀርበው የሚያስተምሩን ክፍሎች ሊያስረዱን የሚፈልጉት፤ በክርስቶስ በኩል መጋረጃው እንደተቀደደና በራሳችን ሥራ ሳይሆን በእርሱ በኩል ያለምንም መከልከል መግባት እንዳገኘን የሚያሳዩን ሲሆን፤ በፍርሃት መቅረብን/ማምለክን የሚያጎሉት ክፍሎች ደግሞ እግዚአብሄር ዛሬም ቢሆን ቅዱስ መሆኑን እንዳንረሳና ከሃጥያት ጋራ እየተጫወትን ልናመልከው እንደማንችል ያስተምሩናል፡፡ እነዚህ ሁለት ሃሳቦች ልክ የሳንቲም ሁለት ገጽታዎች አድርገን ልንመለከታቸው እንችላለን፡፡
7. በቁ28 ላይ አምልኮን በተመለከተ የተዘረዘሩት ነገሮች፤ ደስ በሚያሰኘው መንገድ፣ በአክብሮትና፣ በፍርሃት እንድናመልከው ነው፡፡ በሮሜ 12፡15-18 መሰረት እግዚአብሄርን ደስ በሚያሰኘው መንገድ ማምለክ ማለት ለወንድሞቻችንና ለእህቶቻችን ስንል ሙብታችንን በሙተው በፍቅር መመላለስ ማለት ነው፡፡
8. ያስተማራቸው እግዚአብሄርን ደስ ማሰኘት እንዴት እንደሚችሉ ነው፡፡ ከዕብ 12፡28 ጋራ ስናየው ይህ የተማሩት ትምህርት እግዚአብሄር የሚቀበለውና ደስ የሚሰኝበት አምልኮን ለማቅረብ ይችላሉ ማለት ነው፡፡
9. ይህንን አነጋገር ስሰማ በመጀመሪያ ወደ አዕምሮዬ የሚመጣው ይቅስ ዮሐ 4፡24 ነው፡፡

## ጥናት ሃያ ሁለት ዕብ 13፡1-8 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ስድስቱ ዓይነት ሰዎች፡ እርስ በእርሳችን፣ ከእንግዶች ጋራ፣ እስር ላይ ካሉት ጋራ፣ በሰው እጅ ከሚንገላቱት ጋራ፣ በትዳራችን ውስጥና፣ በግል ራሳችንን አስመልክቶ፡፡ ከላይ ወደታች ሲታይ ጸሃፊው እያጠበበው ሰፋ ካለው ክልል ወጥቶ ወደ ትዳር፣ ከዚያም ወደ ግል ህይወታችን ሲመጣ እንመለከታለን፡፡
2. የመጀመሪያዎቹ በእስር ያሉት ሲሆኑ፣ ሌላዎቹ ደግሞ በሰው እጅ የሚንገላቱት ናቸው፡፡ ለነዚህ ለሁለቱም ዓይነት ሰዎች እንድናስባቸው የሚያስጠነቅቀን መንገድ እኛ ራሳችን በሁኔታው ውስጥ እንደምናልፍ አድርገን እንድናደርገው ነው፡፡
3. ጋብቻን አስመልክቶ በቁ4 ላይ የሰጣቸው ሁለት ትዕዛዞች፡ ባብቻ በሁሉም ዘንድ ክቡር እንዲሆንና፤ በኝታውም ደግሞ ንጹህ እንዲሆን ነው፡፡ እነዚህን ባለመታዘዝ በአመንዝረኝነትና በሴሰኛነት በሚኖር ላይ እግዚአብሄር እንደሚፈርድ ይነግረናል፡፡ ይህንን ስናይ እግዚአብሄር ለጋብቻ ትልቅ ሥፍራ እንደሚሰጥና ራሱን ለፍርድ ለማስገባት ፈቃደኛ የሆነበት ነገር መሆኑን እመለከታለሁ፡፡
4. ዕብ 13፡5 ባለን ነገር ረክተን እንድንኖር ሲመክረን ለዚህም ማደፋፈሪያ አድርጎ ያቀረበልን የእግዚአብሄርን የተስፋ ቃል ነው፡፡ በፊሊ. 4፡12-13ትም ውስጥ የምንመለከተው ይህንን መጽሃፍ ቅዱሳዊ እውነት ሃዋርያው በህይወቱ ተግባራዊ እንዳደረገው ሲሆን ለዚህም ሃይል የሆነው እግዚአብሄር እንደሆነ ይነግረናል፡፡
5. ይህ ሰው ቀጥሎ የተናገረውን ነገር ማለትም ‹‹ጌታ ረዳቴ ነው አልፈራም›› የሚለውን በድፍረት መናገር የቻለው ከላይ በቁ5 ላይ እግዚአብሄር እርሱ ራሱ የተናገረው የተስፋ ቃል ስለነበረ ሳያወላውልና ሳይፈራ በሙሉ ልቡ መናገር እንደቻለ እናያለን፡፡
6. የተሰጡን ሶስት መመሪያዎች፤ 1) የእግዚአብሄርን ቃል የነገሩንን መሪዎቻችንን እንድናስብ፣ 2) የኑሯቸውን ፍሬ እንድንመለከትና 3) በእምነታቸው እንድንመስላቸው ነው፡፡ በቁ3 ላይ አስቧቸው ሲል በጸሎትም ሆነ ባስፈላጊው ነገር ሁሉ የምናደርገውን ድጋፍ ሲያመለክት፣ በቁ7 ላይ ያለው አስቧቸው ግን እንድናስታውሰው የሚያስፈልገንን ነገር ለማሳሰብ እንጂ እንደሌሎቹ ከእርዳታ አንጻር የተነገረ ቃል አይደለም፡፡
7. የእነዚህ ሰዎች የኑሮ ፍሬ ሆነን የተነገርነው እኛ ራሳችን ነን፡፡ እነርሱ የወንጌልን እውነት ባይነግሩን ዛሬ ላለንበት ነገር አንበቃም ነበረ፡፡
8. እነዚህ ሰዎች ያመኑት ነገር፤ የእግዚአብሄር ቃል ወይም ኢየሱስ ክርስቶስ ዛሬም በወንጌሉ እውነት የሰዎችን ህይወት መለወጥ እንደሚችል በማመን ቃሉን ሊነግሩን መድፈራቸውን ነው፡፡ እኛንም በእምነታቸው ምሰሏቸው ሲለን እነርሱ እግዚአብሄር ሊለውጣቸው ይችላል ብለው በእምነት ወንጌልን እንደነገሯችሁ፤ እናንተም ደግሞ በዚያው እምነት ተሞልታችሁ ለሌሎች ወንገልን ንገሩ ማለቱ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ አለመለወጡ ያኔ እነርሱን የረዳና የተጠቀመባቸው ጌታ፤ ዛሬም እኛን ሊረዳና ሊጠቀምብን ይችላል ማለት ነው፡፡
9. እያንዳንዱ በራሱ መንገድ መልስ ይስጥበት፡፡

## ጥናት ሃያ ሶስት ዕብ 13፡9-16 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ሰዎቹን በዚህ ክፍል እየመከረ ያለው በልዩ ልዩ እንግዳ ትምህርት እንዳይወሰዱ ነው፡፡ ልባችን ሊጸና የሚገባው በእግዚአብሄር ጸጋ እንጂ በምግብ እንዳልሆነ አያለሁ፡፡
2. በቆሮንቶስ ውስጥ የምንመለከታቸው ጥቅሶች ካህናቱ የመስዋዕቱን ስጋ ሊበሉ እንደተፈቀደላቸው ሲሆን በዚህ ክፍል ግን እነዚህ ሰዎች በመስቀሉ ላይ የተሰቀለውን መስዋዕት ለሃጥያታቸው ስርየት ካልተቀበሉት ካህናት መሆናቸው ብቻ ከመስዋዕቱ ሊካፈሉ እንደማይችሉ ያስረዳል፡፡ ይህ የቀራንዮ መስዋዕት ከመስዋዕቶች ሁሉ ይለያል፡፡
3. ‹‹ከከተማው በር ውጭ›› ወይም ‹‹ከሰፈር ውጭ›› የሚለው ወንጀለኞችና ሃጥያተኞች የሚቀጡበት ሥፍራ እንደሆነ እመለከታለሁ፡፡ ኢየሱስም በዚህ ስፍራ መከራን መቀበሉ እንደ ወንጀለኛና እንደ ሃጥያተኛ እንደተቆጠረ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ኢሳ 53ትን ማነበብ ይቻላል፡፡
4. መከራን ስለተቀበለበት ምክንያት ክፍሉ የሚያረጋግጥልን ህዝቡን ሊቀድስ እንደሆነ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች የተጠየቁት አንድ ነገር እርሱ የተሸከመውን ውርደት ተሸክመው ከሰፈር ውጭ ወደ እርሱ እንዲወጡ ነው፡፡
5. አንደኛው ዘወትር ምስጋናን እንድናቀርብ ሲነግረን ሌላው ደግሞ ስለሁሉም ነገር ምስጋናን እንድናቀርብ ይነግረናል፤ ስለዚህ እነዚህን ሁለት ክፍሎች በአንድነት ስናይ ለእግዚአብሄር ምስጋናን ማቅረብ የሚኖርብን ስለሁሉም ነገር እንደሆነና ይህንንም ማድረግ የሚገባን ያለማቋረጥ ወይም ዘወትር እንደሆነ እንማራለን፡፡ በዚህ ክፍል ምስጋናን ከእኛ አንደበት የሚወዘጣ ‹‹መስዋዕት›› እንደሆነ ነው የተነገረው፡፡
6. ሶስት ዓይነት መስዋዕቶች ይታዩኛል፡፡ እነዚህም ሀ) ምሥጋናን ዘወትር ማቅረብ፣ ለ) መልካምን ማድረግና ሐ) ያለንን ለሌሎች ማካፈል ናቸው፡፡ እነዚህ መስዋዕቶች እግዚአብሄር ደስ የሚሰኝባቸው መስዋዕቶች ተብለው ነው የተነገሩት፡፡
7. ከሰፈር ውጭ የሚገኘው፤ የቆሸሸ፣ ነፍሰ ገዳይ፣ በሽተኛ፣ ተሳዳቢ፣ የሞቱና ህይወት የሌላቸው ነገሮች የሚገኙበት ሲሆን፤ በሰፈር ውስጥ ግን፡ ምቾት፣ እርጋታና የመሳሰለው ሁሉ የሚገኝበት ሥፍራ ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ሁለቱ በምንም የማይገናኙ ትልቅ ልዩነት ያላቸው ቦታዎች ናቸው፡፡
8. በእኛ ህይወት በሰፈር ውስጥ የሚለውን የተደላደለ ሥራችንን፣ የተሟሟቀ ኑሯችንን፣ የሞቀወን ቤታችንን፣ የተመቻቸ ሃሳብ የሌለበትን ምቾት ሁሉ ይጠቀልላል፤ ኢየሱስ ወዳለበት ከሰፈር ውጭ እንውጣ ሲለን ወደነዚያ ተሳዳቢዎች፣ ወደሞቱት፣ በሽተኞች ወደሆኑት፣ ወደ ቆሸሹትና፣ ወደነፍሰ ገዳዮቹ ወደሚገኙበት እንሂድ ማለቱ ነው፡፡

# ጥናት ሃያ አራት ዕብ 13፡17-25 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. የታዘዝነው መሪዎቻችንን እንድንታዘዝና እንድንገዛላቸው ነው፡፡ ለዚህም የተሰጠን ምክንያት፤ እነርሱ የሚያስጠይቃቸው በመሆኑ ስለነፍሳችን ስለሚተጉ ነው፡፡
2. ለመሪዎቻችን አለመታዘዝና አለመገዛታችን የሚያስከትላቸው ነገሮች፡ በመጀመሪያ ደረጃ ሥራቸውን የሚያከናውኑት በደስታ መሆኑ ይቀርና ልባቸው በሃዘን ተሞልቶ ይሆናል፤ ሌላው ግን የእነርሱ ማዘን ብቻ ሳይሆን ለእኛም ለተገልጋዮቹ ስለማይበጀን ነው፡፡ በክፍሉ መሰረት የመሪዎቻችን ዋነኛ ሃላፊነት ሆኖ የቀረበው የነፍሳችንን ነገር መከታተል መሆኑን እናነባለን፡፡
3. እነዚህ ቃላት በሙሉ ቤተክርስትያንን የሚመራው አንድ ሰው እንዳልሆነና ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች እንደሆኑ አያለሁ፡፡ ከመሪዎች የሚጠበቀው ሃላፊነቱ እንደሚያስጠይቃቸው ሆኖ ማገልገል፣ ስለምዕመናን ነፍስ መትጋትና ሥራቸውን በደስታ መስራት ሲሆን፤ ከምዕመናን የሚጠበቀው ደግሞ ለመሪዎች መታዘዝና መገዛት ነው፡፡
4. ጸሃፊው የሚጠይቀው ነገር ጸሎትን ነው፡፡ ከእነዚህ ክፍሎች የምማረው የአገልግሎቱ መልክ ቢለያይም ቅዱሳን እርስ በእርስ የሚገላገሉ እንጂ የተወሰኑ ሰዎች ብቻ የሚያገለግሉ ሌሎች ደግሞ ተቀምጠው ሁልጊዜ የእነርሱ ተገልጋዮች መሆን እንደማይኖርባቸው እማራለሁ፡፡
5. በአንባቢዎቹ ህይወት እንዲፈጸሙ የሚፈልጋቸው ሁለት ነገሮች፤ የእግዚአብሄርን ፈቃድ እንዲያደርጉ በመልካም ነገር ሁሉ እንዲያስታጥቃቸውና፣ እርሱን ደስ የሚያሰኘውን በክርስቶስ በኩል በእነርሱ እንዲያደርግ ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ነገሮች የሚደጋገፉት፡ የመጀመሪያው እግዚአብሄር በህይወታቸው አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ፈቃዱን ማድረግ መፈለግን ሁሉ ጨምሮ በውስጣቸው እንዲሰራ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ እርሱን ደስ ሊያሰኝ የሚችል ነገር የሚሰራው በራሱ በእግዚአብሄር ስለሆነ በመንፈሱ እንዲሰራው ማለት ነው፡፡
6. ይህ አነጋገር ከላይ ካለው ሃሳብ ጋራ የሚያያዘው በእኛ ህይወት ምንም ዓይነት ድንቅና ተዓምር የሆነ ነገር ቢከሰትም በራሳችን የሰራነው ነገር እንዳልሆነ፣ ፊሊ. 2፡13 እንደሚነግረን መፈለግንም ማድረግንም በእኛ የሰራ እርሱ ስለሆነ ክብሩ ሁሉ ለእርሱ መሆን እንዳለበት ሲነግረን ነው፡፡
7. የጢሞቲዎስ በዚህ ቦታ መጠቀስ ጸሃፊው ሃዋርያው ጳውሎስ ሊሆን ይችላል ወደሚለው ሃሳብ ይጠቁማል፤ ምክንያቱም ጢሞቲዎስ በአብዛኛው አገልግሎቱን ሲያገለግል የነበረው ከጳውሎስ ጋራ ስለሆነና በሌላ ሥፍራም እንደዚሁ ተመሳሳይ አባባል እንዳለ ይነበባል፡፡
8. ሰላምታው እንዲደርስለት የሚጠይቀው ለመሪዎችና ለቅዱሳን ሁሉ ነው፡፡ ምዕመናንን በሁለት መልክ ነው ከፍሎ የሚያየው፤ ይኸውም መሪዎችና ቅዱሳን በሚል ነው፡፡
9. ‹‹አገልጋይና ተገልጋይ›› ‹‹አገልጋይና ተራ ምዕመን›› የሚሉት ይገኙበታል፡፡ የእነዚህ ዓይነት መጠሪያዎች አደገኛነታቸው፤ በመጀመሪያ ደረጃ አንዳንዶች ራሳቸውን የሚገለገሉ ብቻ አድርገው በመቁጠር ዕድሜልካቸውን በአገልግሎት ሳይሳተፉ እንዲኖሩ ያበረታታል፤ ሌላው ደግሞ ‹‹ተራ ምዕመን›› የሚለው አነጋገር በቤተ ክርስትያን እያገለገሉ ያሉት በሚታይ አገልግሎት ውስጥ ካልተሳተፉት የተሻሉ እንደሆኑ ያስመስላል፤ እነዚህ ሁለቱም በቃሉ ሲመዘኑ የተሳሳቱ መሆናቸው ግልጽ ነው፡፡